በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ ለአምላክ አሜን።

የሰው ልጅ ክብር በስነ-ፍጥረት

በግቢ ጉባኤያት አገልግሎት ማስተባበሪያ

ለግቢ ጉባኤያት

ትምህርታዊ ስብከት

ማስተማሪ ተዘጋጀ

ታህሳስ 2014 ዓ.ም

ሥነ ▬ ፍጥረት

መግቢያ፡- የሥነ ፍጥረት ትምህርት በነገረ ሃይማኖት ውስጥ አንዱ የትምህርት ክፍል ሲሆን በአጠቃላይ የዚህን ዓለም ካለ መኖር ወደ መኖር መምጣትና የአስገኚውን ማንነት ለማወቅ ይረዳል። የሰው ልጅ ሁሉ የሥ ፍጥረትን

ትምህርት አስቀድሞ ካልተረዳ ስለራሱም ጥያቄ ይኖረዋልና ገባሬ ኩሉ የሆነውን እግዚአብሔር እግዚአብሔርን ሊያውቀው ቀርቶ ራሱንም አያውቅም። በዙሪያው አብረውት የሚኖሩ ሌሎች ፍጥረታትም ለምን ዓላማ እንደሚኖሩ አይረዳም። ስለሆነም ሥነ ፍጥረትን መመራመር ለሰው የተሰጠ ሥልጣን በመሆኑ ሰዎች ሊመራመሩበትና ሊያጠኑት የሚገባ የትምህርት መስክ ነው። ሥነ ፍጥረትን የሚያምኑትም የማያምኑትም ሊያጠኑት ይችላሉ ከጥናቱ የሚገኘው ውጤት ግን አይቀየርም ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ፍጥረት አሁን ያለውን ኩነተ ኅልውና እንደያዘ ፈጥሮታልና። በዚህ ጽሑፍም በኅላ በተረዳ ስለ ሥነ ፍጥረት ሊቃውንውንተ ቤተ ክርስቲያን ከተናገሩት በተረዳነው ልክ በጣም በትንሹ በመውሰድ የዓለም ሊቃውንት በተለያየ ጊዜ እየተነሱ ስለ ሥነ ፍጥረት የተናገሩትን ከንቱ ፍልስፍና ለማሳየትና በዚህ ጉዳይ ላይ የተሻለ ጥናትና ምርምር ለማድረግ መንገድ ለመጠቆም ይህቺን አጭር ጽሑፍ አቅርበናል።

የጽሑፉ ዓላማ፦ የሥነ ፍጥረትን ካለመኖር ወደመኖር መገኘት፣ ነገረ ኅልውናቸውንና ፍጻሜያቸውን በመግለጥ አስገኚው፣ አኗሪውና የሚያሳልፈውም እግዚአብሔር መሆኑን ማሳወቅ ነው።

፩. የሥነ ፍጥረት ካለመኖር ወደ መኖር መምጣት

፩.፩. ትርጉም፦ “ሥነ - ፍጥረት” ማለት ያማረ ፍጥረት ማለት ነው። እንዲህ የተባለበት ምክንያት “ወርእየ እግዚአብሔር ኪሎ ዘፈጠረ ከመ ሠናይ” ተብሎ በዘፍጥረት ላይ በብዙ ቦታ የተገለፀውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት በማድረግ ነው። ይህም የሚያስረዳን ፍጥረት ሁሉ ተፈላጊና ያማረ መሆኑን ነው።

<u>፩.፪. የሥነ - ፍጥረት ዓላማዎች</u>

1. እግዚአብሔር ስሙ እንዲመሰገን፦ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ከፈጠረባቸው ዓላማዎች መካከል አንዱ ሲሆን ፍጥረታት ከመፈጠራቸው በፊት እግዚአብሔር አይመሰገንም ነበር ማለት ግን አይደለም ታዲያ ፍጥረታት በሌሉበት ማን ያመሰግነው ነበር ቢሉ ባሕርይውን ባሕርይው ያመሰግነው ነበር ይህ ማለት እግዚአብሔር በባሕርይው የተመሰገነ ነው ማለት ነው። ይህንንም “እምቅድመ እፍጥር ኩሎ ፍጥረተ ስብሐትየ ምስሌየ ውእቱ” ብሎ ራሱ እግዚአብሔር መናገሩን መሰረት በማድረግ “እምቅድመ ይፍጥር መላእክተ ለቅዳሴ አኮ ዘተጸርዐ ስብሐተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አላ ምሉእ ውእቱ” ብለው ፫ቱ ምዕት በቅዳሴያቸው ቁጥር ፴፭ ላይ ገለፀውታል። እንዲህ ከሆነ ታዲያ ፍጥረታትን ለምን ፈጠረ ቢሉ ክብሩ በባሕርዩ ብቻ እንደቀረ አውቆ ይኸን ዓለም ፈጠረው። ሰውና መላእክትን ስሙን ለመቀደስ ክብሩን ለመውረስ ሌሎችን ፍጠረታት ለአንክሮ ለተዘክሮ ለምግበ ሥጋ ለምግበ ነፍስ ፈጠረ። እነዚህን ፍጠረታትም ስለ አምስት ነገር ፈጥሯቸዋል፣ “ከሀሊነቱን፣ ባዕልነቱን፣ ርኩበነቱን፣ ዘኢይትረከብነቱን፣ ራትዕነቱን ለመግለጥ። ከሀሊነቱ ይህን ዓለም እም ኅበ አልቦ ኅበ ቦ አምጥቶ መፍጠሩ፣ ኃላም እም ኅበ ቦ ኅበ አልቦ ማሳለፉ፣ ባዕልነቱ ዛሬ ባለጸጋ ብዙ ሰው ጠርቶ ሲያበላ ሲያጠታ ጠጅ ላለው ጠጅ ሥጋ ላለው ሥጋ የሰጠ እንደሆነ ባለጸግነቱ እንዲታወቅ ጌታም ግዝፋኑን አራዊትን እንስሳትን ሰውን ፍጥሮ ግዙፍ ምግብ ዘርእን ተክልን መመገቡ ረቂቃኑን መላእክትን

ነፍስን ፈጥሮ መንፈሳዊ መግብ ቅዳሴን በመመገቡ ባዕልነቱ ይታወቃል፣ ርኩብነቱ በሥነ ፍጥረት ይመረመራል፣ ወዘኢያስተረኢ እግዚአብሔር እምፍጥረተ ዓለም ይትዐወቅ በፍጥረቱ እንዲል፣ ዘኢይትረከብነቱ ባሕርይው አይመረመርምና፣ ራትዕነቱ ዲያብሎስ ቢክድ በንስሐ እንዳይመለስ ዓውቆ ቦታውን ለአዳም ሰጥቶበታል አዳም ቢበድል በንስሐ እንዲመለስ ዐውቆ ቦታውን ለመላእክት አስጠብቆለታል፣ ወአዘዞሙ ለኪሩቤል ወለሱራፌል ዘውስተ እደዊሆሙ ሰይፈ እሳት እንተ ትትመያየጥ ከመ ይዕቀቡ ፍኖተ ዕፀ ሕይወት እንዲል ትርጓሜ ዘፍጥረት ዳግመኛም "አሠርተ አሠርተ ኮነ ነገደ መላእክት ወእም አሠርቱ አሠርቱ ነገደ መላእክት ወድቀ አሐዱ ወተውህበ መንበሩ ለእጓለ እመሕያው ተስእ ወተስእተ ነገደ ኮነ።" እንዳሉ ሊቀ ሊቃውንት ያሬድ ሽፈራው (መጽሐፈ ግስ ወሰዋስው መርጥመጻሕፍት ገጽ ፱፻፴፱) እነዚህም የእግዚአብሔር የባሕርይው መገለጫዎች ናቸው።

2. ህልውናው ይታወቅ ዘንድ፦ እግዚአብሔር የሁሉ አስገኝ የሁሉ ፈጣሪ መሆኑ የሚታወቀው በቃል ወይም በጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በሥነ ፍጥረቱ ነው። ያለ አስገኝ የተገኘ ያለ ፈጣሪ የተፈጠረ ፍጡር የለም ስለዚህ ፈጥረት ሁሉ አስገኝ፣ ፈጣሪ፣ ባለቤት አለው እርሱም እግዚአብሔር። እግዚአብሔር ህለዎት ከሚታወቅባቸው ፍጥረታት መካከል ሰው ዋነኛው ነው ይኼውም ይታወቅ ዘንድ "ወገብሮ እግዚአብሔር ለዕጓለ እመሕያው በአምሳለ እግዚአብሔር" ዘፍጥ ፩÷፳፯ በማለት ገልጾታል። የሌሎች ፍጥረታት ኩነተ ህልውናም እግዚአብሔር መኖሩ የሚታወቅባቸው መሆናቸው በላይኛው ጽሑፍ ላይ ተገልጧል።

3. ምግበ ሥጋ ምግበ ነፍስ ይሆኑ ዘንድ፦ እነዚህ ፍጥረታት እግዚአብሔር ባዕለ ኩሉ መሆኑ መሆኑ የሚታወቅባቸው ፍጥረታት ናቸው። ከፈጠራቸው ፍጥረታት መካከል እንስሳት፣ እፀዋት፣ አዝርዕትና አትክትልት ይገኙበታል። ለምሳሌ ከአዝርዕት መካከል ስንዴን ብንወስድ ለነፍስ ሕብስተ ሕይወት ለሥጋ ህብስተ ሥጋ ሆኖ ሲያገለግል ከአትክልት መካከል ወይንን ብንወስድ ለነፍስ ስተየ ሕይወት ለሥጋ ስተየ ሥጋ ሆኖ ያገለግላል።

4. መማሪያና ማስተማሪያ ይሆኑ ዘንድ፦ ሁሉም ፍጥረታት ልዩ ልዩ በሆነ መንገድ ጠቀሜታ እንዳላቸው አውቆ እግዚአብሔር እንደፈጠራቸው ከላይ ተጠቁሟል። እነዚህ ፍጥረታት በተለይ ለሰው ልጅ ለመንፈሳዊም ለሥጋዊም ዕውቀት መሠረቶች ናቸው። ይኼውም ይታወቅ ዘንድ ፀሐይን ለሥላሴ አንድነትና ሦስትነት፣ እሳትን ለመለኮት፣ ብርሃንን ለጌታ፣ ነፋስን ለመንፈስ ቅዱስ ወዘተ ምሳሌ አድርገን የምንማርባቸው መንፈሳዊ ዕውቀትን የምናገኝባቸው መሆናቸውን የሚገልጽ ሲሆን የሰው ልጅ ለሳይንስ ምርምር፣ ለመድኃኒት ቅመማ የአየር ንብረት ሚዛንን ለመጠበቅ የሚያገኘው ዕውቀት ከሥነ ፍጥረታት ከሚገኙ ሥጋዊ ዕውቀቶች ምሳሌዎች ናቸው።

፩.፫. የሥነ ፍጥረት መገኛ

እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን ያስገኘው በሁለት መንገዶች ነው። እነዚህም

1. እም ኀበ አልቦ ኀበ ቦ ካለመኖር ወደ መኖር
2. ግብር እም ግብር ከተፈጠረው የተፈጠሩ

እም ኀበ አልቦ ኀበ ቦ የተፈጠሩ የዕለተ እሁድ ፍጥረታት ሲሆኑ ከዕለተ ሰኞ እስከ ዕለተ ዓርብ የተፈጠሩ ፍጥረታት ደግሞ እምግብር ኀበ ግብር የተገኙ ናቸው። እነዚህንም እግዚአብሔር በሦስት መንገድ ፈጥሯቸዋል።

1. በሐልዮ
2. በነቢብ ናቸው።
3. በገቢር

እነዚህ ከላይ ያስቀመጥናቸው ሦስቱ እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረበትን ሁኔታ በቀላሉ እንድንረዳው እንጂ እግዚአብሔር በሐልዮ ጊዜ ከነቢብ ተለይቶ በነቢብ ጊዜ ከገቢር ተለይቶ ወይም ገቢርን ትቶ በሐልዮ ይሠራል የሚል ሰውኛ ሐሳብ የሚቀርብበት አይደለም። ይህም ይታወቅ ዘንድ “ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን በርሃን” ላለው ስለምን ሰባቱን በአርምሞ በርሃንን በነቢብ ፈጠረው ቢሉ፡

- በመላእክት መካከል በተፈጠረው ምንት ንሕነ “እም አይቴ መጻዕነ ወመኑ ፈጠረነ ወሚመ በበርእስነኑ ተፈጠርነ?” በሚል ጥያቄ ምክንያት “እነ ፈጣሪሆሙ ለእሉ ፍጡራን” የሚል መዝገበ አመጻ ሳጥናኤል ባወጀው የክህደት ትምህርት ምክንያት በተፈጠረው ውዝግብ መላእክት ጨርሰው ሳይክዱ ለይኩን ብርሃን ብሎ ብርሃንን ፈጠረላቸው።
- አንድም በአርምሞም በነቢብም መፍጠር ይቻለኛል ሲል መናፍቃን በአርምሞ እንጂ በነቢብ፣ በነቢብ እንጂ በአርምሞ መፍጠር አይቻለውም ባሉ ነበርና ምክንያት ለማጥፋት፤
- አንድም ቀድሞ ሰማዕያን መላእክት አልነበሩምና ሰባቱን በአርምሞ ፈጠረ። አሁን ግን ሰማዕያን መላእክት አሉና ብርሃንን በነቢብ ፈጠረ። ያውም ቢሆን የልቡና ነቢብ ነው። ተብሎ ተተርጎሞ እናገኘዋለን።

1. በሐልዮ የተፈጠሩ ፍጥረታት
    - ሰባቱ ሰማያት
    - አራቱ ባሕርያት (ነፋስ፣ እሳት፣ ውኃ፣ መሬት)
    - መላእክት
    - ጨለማ
2. በነቢብ የተፈጠሩ ፍጥረታት
    - ብርሃን
    - አዝዕርት
    - አትክልት ናቸው።
    - ዕፀዋት
    - ፀሐይ
    - ጨረቃ
    - ከዋክብ
    - አእዋፍ
    - እንስሳት

- አራዊት

3. በገቢር የተፈጠረ
    - የሰው ልጅ

፪.፭. በየዕለቱ የተፈጠሩ ፍጥረታት

ቀጥታ ይህንን ጉዳይ ከማየታችን በፊት ስለ ሥነ ፍጥረት በአንዳንድ ወገኖች የሚባለውን የተወሰነ ሐሳብ በማንሳት እንጀምራለን።

1. “እግዚአብሔር መላውን ዓለም (ሥነ-ፍጥረት) በአንድ ቀን ፈጥሮታል። ሙሴ ስድስት ቀናት ያደረገው የእግዚአብሔርን ድንቅ ጥበብ ለማሳየት ነው” የሚሉ አሉ።
2. ሌሎች ደግሞ “እግዚአብሔር የፍጥረትን ንጥረ ነገሮች ከፈጠረ በኋላ በሚቀጥሉት ቀናት ሥነ ሥርዓት እንዲይዙ አደረገ” ይላሉ።
3. “ሥነ ፍጥረት እንደተፈጠረባቸው የተጠቀሱት ስድስት ዕለታት ቀናት ሳይሆኑ በብዙ ሽህ ዘመን የሚቆጠሩ ዓመታት ናቸው” የሚል ንድፈ ሐሳብ የሚያቀርቡም አልጠፉም።
4. በዚህ ዘመንም ስለ ዓለማት ጥንትና መገኛ እና ስለ ወደፊት ዕጣ ፈንታቸው የሚያጠኑ ፈላስፎች ብዙ ናቸው።

የስድስቱ ዕለታት ሥነ ፍጥረታት

ከላይ አበክረን እንዳየነው የተለያዩ የሳይንስና የፍልስፍና ሰዎች የእግዚአብሔርን ህልውና በተመለከተ የሚጠራጠሩ ወይም የማያምኑ በመሆናቸው ፍጥረታቱንም ከሳይንስ ወይም ከፍልስፍና አንጻር ለማየትና አማንያንንም ለማጠራጠር የሚጠቀሙት ከንቱ ሐሳብ ነው እንጂ እግዚአብሔር ፍጥረታትን እንዴት፣ ከመቸ አስከ መቸ እና ለምን እንደፈጠራቸውማ ሌላውን እንኳ ባናነሳ ከአምስቱ መጻሕፍተ ኦሪት አንዱን ኦሪት ዘፍጥረትን ጠንቅቆ መረዳት ከበቂ በላይ ማስረጃ ነው። እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ የጨረሳቸው በአንድ ቀን ነው የሚለው በየትኛው አቆጣጠር ከየትኛው መጽሐፍ ሊገኝ ይችላል? ሙሴስ ቢሆን እግዚአብሔር አንድ ቀን ፈጥሮ ያጠናቀቃቸውን ፍጥረታት ስድስት ቀን ስለማድርጉ የትኛው ታሪክ ላይ ገልፆታል? እግዚአብሔር በአንድ ቀን ያጠናቀቃቸውን ፍጥረታትስ በስድስት ቀናት ፈጠራቸው ማለት እግዚአብሔርን እንደ ደካማ በቶሎ ሥራውን የማያጠናቅቅ እንደማለት ካልሆነ በቀር የእግዚአብሔርን ድንቅ ጥበብ መግለጥ ሊሆን የሚቸለው እንዴት ነው። ሌሎቹስ ቢሆኑ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ለመጨረስ ብዙ ሽህ ዘመናትን ፈጅቶበታል ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? እግዚአብሔር ሥራዎችን ለመሥራት የሰው ያህል እንኳ የማይፈጥን አድርጎ መቁጠር በእውነቱ የእነዚህን ሰዎች የአስተሳሰብ ድህነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። በሌላ በኩል እኛ የሰው ልጆች ከፍጥረታት መካከል መሆናችንን መዘንጋት የለብንም ይሁንና ግን በሌሎች ፍጥረታት ላይ ከእግዚአብሔር ሥልጣን ስለተሰጠን እንጠቀምባቸዋለን፣ እንጠብቃቸዋልን በፍጥረታት ላይ

የመመራመር ሥልጣንም አለን እግዚአብሔር እንዴት እንደፈጠራቸው ለምን ዓላማ እንደፈጠራቸውና መቸ እንደፈጠራቸው በቅዱሳት መጻሕፍት የተመዘገበውን አንብቦ ተምሮ ከማወቅ ወጪ የእግዚአብሔርን አሠራር አመረምራለሁ ማለት ግን ውድቀትን ሞትን ያስከትላል እንጂ ጥቅም የለውም። ስለሆነም እግዚአብሔር ሥነ ፍጥረትን እሁድ ጀምሮ በስድስተኛው ዕለት ዓርብ ፈፀመ በሰባተኛው ዕለትም ከሥራው ሁሉ አረፈ ይለናል መጽሐፍ ቅዱስ። በስድስቱ ዕለታት የተፈጠሩ ፍጥረታት ማን ማን ናቸው ቢሉ፡-

1. <u>በዕለተ እሁድ የተፈጠሩ ፍጥረታት፡-</u>

በዚህ ዕለት ስምንት ፍጥረታት ተፈጥረዋል እነሱም፡-

- ፩. ሰባቱ ሰማያት
- ፪. መሬት
- ፫. ውኃ
- ፬. እሳት
- ፭. ነፋስ
- ፮. ጨለማ
- ፯. መላእክት
- ፰. ብርሃን

ናቸው።

ከዚህም ሰባቱን በአርምሞ ፈጥሮ ብርሃንን በነቢብ ፈጥሮታል ይህንም ማድረጉ በአርምሞም በነቢብም መፍጠር ይቻለኛል ሲል። አንድም ቀድሞ ሰማዕያን መላእክት አልነበሩምና ሰባቱን በአርምሞ ፈጠረ፤ አሁን ግን ሰማዕያን መላእክት አሉና ብርሃንን በነቢብ ፈጠረ። ያውስ ቢሆን በፊት ጨለማን ፈጥሮ ኋላ ብርሃንን ስለምን ፈጠረ ቢሉ በፊት ብርሃንን ፈጥሮ በኋላ ጨለማን ቢፈጥር ሠናይ አምላክ ብርሃንን ቢፈጥር እኩይ አምላክ ጨለማን ፈጠረ ይሉ ነበርና ከመናፍቃን ምክንያት ለማጥፋት። አንድም የሚያልፈውን በፊት የማያልፈውን በኋላ መፍጠር ክፉውን በፊት በጎውን በኋላ ማምጣት ለጌታ ልማዱ ነውና ጨለማውን በፊት ፈጥሮ ብርሃኑን በኋላ ፈጠረው።

ከሰባቱ ፍጥረታትስ የሰማይና የምድርን ነገር ተናግሮ የሌሎችን ያልተናገረው ስለምን ነው ቢሉ በሰማይና በምድር ያሉ ከሆነ ብሎ። አንድም ሰሎሞን እሳተ ጎዩለ፣ ነፋሰ ጎዩለ አው ማየ ጎዩለ እንዲል እነዚህ ኃያላን ናቸው አንስቷቸው ቢሆን መናፍቃን እነሱ ኃይል ሆነውት ፈጠረ ባሉት ነበርና ከመናፍቃን ምክንያት ለማጥፋት። አንድም ሁሉን አሁን ወደ ፊት ያመጣቸዋል የጨለማን ተፈጥሮ ወጽልመት መልዕልተ ቀላይ ብሎ፤ የነፋስን ተፈጥሮ ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ ብሎ፤ የመላእክትን ተፈጥሮ ወአዘዘሙ ለኪሩቤል ወለሱራፌል ብሎ ያመጣዋል።

2. <u>የዕለተ ሰኑይ ፍጥረታት</u>

በዕለተ ሰኑይ የተፈጠሩት ፍጥረታት አራት ሲሆኑ እነዚህም በዕለተ እሁድ ከተፈጠረው ከውሃ ግብር እም ግብር የተፈጠሩ ናቸው። እነዚም፡-

- ፩. የምናየው ሰማይ (ጠፈር፣ ሥዕለ ማይ)
- ፪. ከጠፈር በላይ የተሰቀለው ሐኖስ
- ፫. በምድር ዙሪያ የተጠመጠመው ውኃ ናቸው።
- ፬. ለምድር ምንጣፍ የሆነው በርባሮስ

“ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩን ጠፈረ ማዕከለ ማይ ከመ ይፍልጥ ማዕከለ ማይ ወማይ ወኮነ ከማሁ” እንዲል በዘፍጥረት ፩÷፮ ያቺ እሁድ በዕለተ ሠርክ ለሰኞ አጥቢያ ብዝኀኒ ወተባዝኀኒ ስፍሒ ወተሳፍሒ ያላት ውኃ ከምድር ጀምራ አስከ ብሩህ ሰማይ ድረስ መልታ ሰፍታ አድራ ውላ ነበር። እግዚአብሔር “ለይኩን ጠፈር በማዕከለ ሰማይ” ብሎ ቢያዝዝ ውኃው ከአራት ተከፈለ። በውኖች መካከል ጠፈር ይሁን፣ በውኃና ውኃ መካከልም ይከፈል አለ። ጠፈርን አደረገ ከጠፈር በታችና ከጠፈር በላይ ያሉትንም ውኖች ለየ እንዲሁም ሆነ፤ ጠፈርንም ሰማይ ብሎ ጠራው።

በማዕከል ያለቺው ሲሦዋ ወኃ እንደ ቤተ ንጉሥ አዳራሽ ጠፈር ተመሠረተች ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ከሰሜን እስከ ደቡብ መልታ ሰፍታ አደረች። በአፎቱ እንደተከተተ ሰይፍ ሆነች።

ስለምን እግዚአብሔር ጠፈርን እንደ ቤተ ንጉሥ አዳራሽ አድርጎ ፈጠረው ቢሉ እንደ ሰቀላ አድርጎ ቢፈጥረው በዕለተ ረቡዕ የሚፈጥራቸው ፀሐይና ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ብርሃናቸውን ወደ ላይ በነዙ በአበሩ ነበር እንጂ ወደ ታች ወደ እኛ ብርሃናቸውን ባልነዙም ባላበሩም ነበር። እንድም እንደ ሰቀላ ቢፈጥረው ዓይናችን ማረፊያ አጥቶ ተስፈንጥሮ በወደቀ ነበርና፤ ለዓይናችን ተስፋ ለሰውነታችን ቤዛ እንዲሆን ብሎ ጠፈርን እንደ ቤተ ንጉሥ አዳራሽ ጎበብ አድርጎ ፈጠረው። የዚህንም ጎብሩን እጅግም ቀይ እጅግም ነጭ አላደረገውም አረጓንዴ ቢጫ አስመስሎ ፈጥሮታል፤ እጅግም ቀይ አድርጎ ቢፈጥረው ለዓይናችን የደቂ ምክንያት በሆነ ነበር፤ እጅግም ነጭ አድርጎ ቢፈጥረው ብርሃኑ ዓይናችንን በበዘበዘው ነበርና አረንጓዴ ቢጫ አስመስሎ ፈጠረው።

ጠፈርን ወደ ታች ሐኖስን ወደ ላይ አድርጎ መፍጠሩ ጠፈር የፀሐይ ሙቀት ሲጸናበት እንዳይፈርስ እንዳይሰበር ብሎ ነው።

3. <u>የዕለተ ሠሉስ (ማግሰኞ) ፍጥረታት</u>

በዕለተ ሠሉስ “ወይቤ እግዚአብሔር ለታብቍል ምድር ሐመልማለ ሣዕር ዘይዘራእ በበዘርኡ ወበበዘመዱ” ዘፍጥ ፩÷፲፩ ብሎ ሙሴ እንደመዘገበው እግዚአብሔር ሰኞ ማታ ለማክሰኞ አጥቢያ በጊዜ ሠርክ ሦስት ፍጥረታትን ፈጠረ። እነዚህም፡-

- ፩. በምሳር የሚቆረጡ እፀዋት
- ፪. በማጭድ የሚታጨዱ አዝዕርት ናቸው።
- ፪. በጥፍር የሚላጡ አትክልት

አንድም በዚህ ዕለት አራት ፍጥረታትን ፈጠር ይልና ዕጸወ ገነትን አራተኛ ያደርጋቸዋል። እነዚህም ብርሃን የማይለያቸው፣ መዓዛቸው ከሩቅ የሚሸት፣ ልቅመዋቸው ሲመልሱ ፍሬ ተክተው የሚገኙ ናቸው። ሦስቱ ፍጥረታትስ

በምን ተለይተው ይታወቃሉ ቢሉ በምሳር የሚቆረጡ እፀዋት እነ ዋንዛን፣ እነ ዝግባን አንድ ወገን፣ በማጭድ የሚታጨዱ እነ ስንዴን እነ ጤፍን እነ ገብስን አንድ ወገን፣ በጥፍር የሚላጡ እነ ሎሚን እነ ትርንጎን እነ ብርቱካን አንድ ወገን አድርጎ በመፍጠሩ ተለይተው ታውቀዋል። የእነዚህም መገኛቸው ከአራቱ ባሕርያት ነው፤ ይህም ይታወቅ ዘንድ በነፋስ ያብባሉ ያፈራሉ፤ "አስመ ነፋስ ያገዝፎ ለፍሬ" እንዲል፣ እንደ ዶግ እንደ ችርንችር ያለውን ሲሰብቁት እሳት ይወጣዋል፣ እንደ ዋርካ እንደ ቁልቋል እንደ ቅንጭብ ያሉትን ሲወጓቸው ደም ይወጣቸዋል፤ ቀርጠው ቢጥሏቸው ፈርሰው በስብሰው አፈር ይሆናሉ።

4. <u>በዕለተ ረቡዕ የተፈጠሩ ፍጥረት</u>

"ወይቤ እግዚአብሔር ለይኩኑ ብርሃናት ውስተ ጠፈረ ሰማይ" እንዲል ዘፍጥረት ፩÷፲፬ ማግሰኞ ማታ ለረቡዕ አጥቢያ እግዚአብሔር በሰማይ የሚገኙ ሦስት ፍጥረታትን በነቢብ ፈጥሯል። እነዚህም፡-

- ፩. ፀሐይ
- ፪. ጨረቃ ናቸው።
- ፫. ከዋክብት

ይህንንም ሊቁ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ በመጽሐፉ አክሲማሮስ ሲያብራ "ወእምዝ አሥአ እግዚአብሔር እሳተ ወነፋሰ በበንስቲት ወገብረ ሰሌዳ ፀሐይ ወዓዲ ነሥአ እግዚአብሔር ነፋሰ ወማየ በበንስቲት ወገብረ ሰሌዳ ወርኅ ወሰሌዳ ከዋክብት" አክ.ዘረብዕ ፪-፫ በማለት እግዚአብሔር የፀሐይን ሰሌዳ ከእሳትና ከነፋስ ፈጠረ ይህም ይታወቅ ዘንድ በእሳትነቷ ታተኩሳለች በነፋስነቷ ትሄዳለች፤ የጨረቃና የከዋክብትን ሰሌዳቸውን ከነፋስና ከውኃ ፈጠረ፤ ይህም ይታወቅ ዘንድ በነፋነታቸው ይሄዳሉ በውኃነታቸው ይቀዘቅዛሉ። በዘፍጥረት ትርጓሜ ላይ አንድም የፀሐይም የጨረቃም ተፈጥሯቸው ከነፋስ ከእሳት ነው እግዚአብሔር ፀሐይን ሙቂ ድመቂ ቢላት ትሞቃለች ትደምቃለች፣ ጨረቃን ድመቂ አትሙቂ ቢላት ትደምቃለች እንጂ አትሞቅም።

"ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር ብርሃነ እምዘዚአሁ ብርሃን መጠነ ኅጠተ ስርናይ" እንዲል አክ.ዘረቡዕ ፭ እግዚአብሔር የስንዴ ቅንጣት የምታህል ብርሃን ወስዶ ለሰባት ከፍሎ አምስቱን ለፀሐይ ሁለቱን ለጨረቃ ቀባቸው፤ ነገር ግን ፀሐይ ብርሃኑ ኃያል ቢሆን ሦስት እጁን ለፀሐይ አስቀርቶ አንዱን እጅ ለከዋክብት፣ አንዱን እጅ ለማያትና ለደመና ቀባቸው። ፀሐይም፣ ጨረቃም፣ ከዋክብትም ብርሃናቸው አሁን የመናየውን ሆነ። ፀሐይንም በቀን አሠለጠነው ጨረቃንና ከዋክብትንም በሌሊት አሠለጠናቸው።

5. <u>የዕለተ ሐሙስ ፍጥረታት</u>

ይህንንም ሙሴ "ወይቤ እግዚአብሔር ለታውፅእ ማይ ዘይትሐወስ ዘቦ መንፈሰ ሕይወት ወአዕዋፈ ዘይሠርሩ መልዕልተ ምድር ወመትሕተ ሰማይ" ብሎ በዘፍጥ ፩÷፳ እንደመዘገበው እግዚአብሔር ረቡዕ ማታ ለሐሙስ አጥቢያ ውኃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ ብሎ ቢያዝዝ፡-

- ፩. በልብ የሚሳቡ አራዊት

- ፪. በክንፍ የሚበሩ አእዋፍ ተፈጥረዋል።
- ፫. በእግር የሚሽከረከሩ እንስሳት

እነዚህም መገኘታቸው ምንም ከባሕር ቢሆን ተፈጥሯቸው ከአራቱ ባሕርያት ነው። ከእነዚህም ከባሕር ተገኝተው በዚያው ጸንተው የቀሩ አሉ፤ አንድ ጊዜ ወደ የብስ አንድ ጊዜ ወደ ባሕር የሚሉ አሉ፤ በረው በረው የሔዱ አሉ፤ ይኼውም ምሳሌ ነው፤ ባሕር የጥምቀት፣ በባሕሩ ጸንተው የቀሩት በክርስትናቸው ጸንተው የሚኖሩ ሰዎች ምሳሌ፣ በረው በረው የሔዱት ወደ ክህደት ወደ ኃጢአት የሔዱ ሰዎች ምሳሌ፣ አንድ ጊዜ ወደ የብስ አንድ ጊዜ ወደ ባሕር የሚመላለሱ አንድ ጊዜ ወደ ሃይማኖት ወደ ጽድቅ አንድ ጊዜ በደ ክሕደት ወደ ኃጢአት የሚመላለሱ ሰዎች ምሳሌ ነው።

ይህስ አይደለም፤ ወባረኮሙ ለክልኤሆሙ በአሐቲ በረከት ይላል ብሎ ሁሉም የበጎ ነው፤ ባሕር የዚህ ዓለም፣ በባሕር ጸንተው የቀሩት በሚስቶቻቸው በባሎቻቸው ጸንተው ቆርበው ጸድቀው አሥራቱን በኩራቱን አውጥተው የሚኖሩ የሰበአ ዓለም ምሳሌ፣ በረው በረው የሔዱት ጎድግዎ ወመነንዎ ለዝ ዓለም ብለው የሚሔዱ የመናንያን ምሳሌ፣ አንድ ጊዜ ወደ የብስ አንድ ጊዜ ወደ ባሕር የሚሉት ተድላ ዓለም ሲጸናባቸው ወደ ዕፀበ ገዳም፣ ዕፀበ ገዳም ሲጸናባቸው፣ ወደ ተድላ ዓለም የሚሉ ሰዎች ሰዎች ምሳሌ ነው።

6. <u>የዕለተ ዓርብ ፍጥረታት</u>

በስድስተኛው ዕለት “ወይቤ እግዚአብሔር ለታውፅእ ምድር ዘመደ እንስሳ ወዘይትሐወስ ወአራዊተ ምድር ዘበበዘመዱ” ዘፍጥ ፩÷፳፬ ዳግመኛም “ወይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ” ዘፍጥ ፩÷፳፮ እንዲል እግዚአብሔር ሐሙስ ማታ ለዓርብ አጥቢያና ዓርብ በነግሕ፦

- ፩. በልብ የሚሳቡ አራዊት
- ፪. በክንፍ የሚበሩ አእዋፍ ተፈጥረዋል።
- ፫. በእግር የሚሽከረከሩ እንስሳት
- ፬. ሰው

የአራዊት የእንስሳትና የአራዊት ከላይ ተገልጧል የሰው ተፈጥሮ ከዚህ ይተነተናል። “ወገብሮ እግዚአብሔር ለዕጓለ እመ ሕያው በአምሳለ እግዚአብሔር” እንዲል እግዚአብሔር አዳምን በራሱ አምሳል በነግህ ፈጠረው። ይህም በዚሁ የመጽሐፍ ክፍል ላይ እንደተተረጎመው ሌሎችን ፍጥረታት በሰርክ ፈጥሮ እሱን በነግህ መፍጠሩ ሰርክ ተከታዮ ጨለማ ነው እነዚያ አላዋቂ ናቸው ሲል የነግህ ተከታዩ ብርሃን ነው የሰው ልጅ አዋቂ ነው ሲል፤ ሌሎችን በፊት ፈጥሮ ሰውን በኋላ መፍጠሩም አንደኛ ሰው ጥያቄ እንዳይኖረው የሚያስፈልገውን አሟልቶ ሰውን ፈጠረው ሁለተኛ በሌሎች ፍጥረታት ክንውን ላይ የእኔ ተሳትፎ አለበት እንዳይል በኋላ ፈጠረው። የሰው ልጅ ተስፋ ትንሳኤ ያለው በመሆኑም ቆሞ እንዲሄድ አድርጎ ፈጠረው ይላል። ዘፍጥ ፩÷፳፯።

“አዳምን ግን ከአራቱ ባሕርያት ብቻ አልፈጠሩትም የማትበላ የማትጠጣ የማትተኛ የማታንቀላፋ ሦስት ግብር የአላት ነፍስ ጨምረው ፈጥረውታል። አዳምም በአካለ ነፍሱና በአካለ ሥጋው መቀዳደም መከታተል የለበትም” አክሲማሮስ ዘዓርብ አንቀጽ ፯።

፪. <u>ፍጥረታዊ ባሕሪያቸው</u>

<u>፪.፩ አራቱ ባሕርያት</u>

በአክሲማሮስ ዘዓርብ “ወአልቦ ፩ ዘኢተፈጥረ ምንትኒ እም፬ቱ ጠባይዓት ዘእንበለ መላእክት ባሕቲቶሙ” እንዳለ ቅዱስ ኤጲፋንየስ ከመላእክት በቀር ከአራቱ ባሕርያት ያልተፈጠረ ፍጥረት የለም። ነገር ግን እነዚህ አራቱ ባሕርያት “ዝኬ ውእቱ ትዕዛዙ ለእግዚአብሔር እሳት ይኄይሉ ለማይ፤ ወማይ ይኄይሉ ለእሳት፤ ነፋስ ይኄይሉ ለመሬት፤ ወመሬት ይኄይሉ ለነፋስ፤ ወነፋስ ይኄይሉ ለማይ፤ ወዘበጦ ከመ ከበሮ በማዕበል - እሳት ውኃን ያፈላዋል ውኃ እሳትን ያጠፋዋል፤ ነፋስ መሬትን ይሸረሽረዋል ይጠርገዋል ይሰነጥቀዋል፤ መሬትም ነፋስን ይጋርደዋል፤ ይገድበዋል፤ ነፋስ ውኃን ይመታዋል እንደ ከበሮ ያስጮኸዋል” እንዳለ አክሲማሮስ ዘእሁድ እነዚህ አራቱ ባሕርያት መስተጻርራን ናቸው ይጣላሉ ይሸናነፋሉ።

እግዚአብሔርም እነዚህን ለማስታረቅ ሦስት ሦስት ግብር ያላቸው እያደረገ ፈጥሯቸዋል “ወገብረ ፮ተ ዘመደ” እንዲል ኩፋሌ ፪÷፰። አራቱ ባሕርያትና ግብራቸውን እንደሚከተለው ዘርዝረናቸዋል።

1. የነፋስ ግብሩ
    - ሞቃትነት
    - ቀዝቃዛነት
    - ጥቁርነት
2. የእሳት ግብሩ
    - ብሩህነት
    - ሞቃትነት
    - ደረቅነት
3. የውኃ ግብሩ
    - ብሩህነት
    - ርጥብነት
    - ቀዝቃዛነት
4. የመሬት ግብሩ
    - ደረቅነት
    - ጥቁርነት
    - ርጥብነት

ናቸው

እግዚአብሔር እነዚህን አራቱን ባሕርያት እንዴት አስታርቋቸዋል ቢሉ፡-

- ❖ ነፋስን በሙቀቱ ከእሳት ጋር፣ በቀዝቃዛነቱ ከውኃ ጋር፣ በጥቁርነቱ ከመሬት ጋር አዋሕዶ አስማምቶ ትቶታል።
- ❖ እሳትን በሙቀቱ ከነፋስ ጋር፣ በብሩህነቱ ከውኃ ጋር፣ በደረቅነቱ ከመሬት ጋር አዋሕዶ አስማምቶ ትቶታል።
- ❖ ውኃን በብሩህነቱ ከእሳት ጋር፣ በርጥብነቱ ከመሬት ጋር፣ በቀዝቃዛነቱ ከነፋስ ጋር አዋሕዶ አስማምቶ ትቶታል።
- ❖ መሬትን በደረቅነቱ ከእሳት ጋር፣ በጥቁርነቱ ከነፋስ ጋር፣ በርጥብነቱ ከውኃ ጋር አዋሕዶ አስማምቶ ትቶታል።

እነዚህን ባሕርያት እግዚአብሔር ለምን ዝቅ ብሎ ሦስት ከፍ ብሎ አራት አላደረጋቸውም አራት ያደረጋቸው ስለምን ነው ቢሉ። እኔም አራቱ ባሕርያት አሉኝ ሲል ነው። የእግዚአብሔር አራቱ ባሕርያትስ ምን ምን ናቸው ቢሉ፡-

- ➢ ፈታሒነት
- ➢ ኃያልነት
- ➢ መንጽሒነት
- ➢ ባዕልነት

ናቸው።

- ➢ ነፋስ ፍሬን ከገለባ ገለባን ከፍሬ ይለያል፤ ጌታም ጻድቃንን ከኃጥአን ኃጥአንን ከጻድቃን ይለያልና ፈታሒ ነኝ ሲል ነፋስን ፈጥሯል። ማቴ ፫÷፲፪-፲፫ ዳግመኛም "የአምር እግዚአብሔር ገቢረ ፍትሕ" እንዲል መዝ ፱÷፲፮።
- ➢ እሳት ኃያል ነው ባሕር ገደል ካልከለከለው ሁሉን አቃጥሎ ያጠፋል ጌታም ቸርነቱ ካልከለከለው ሁሉን ቢያጠፋ ይቻለዋልና ኃያል ነኝ ሲል እሳትን ፈጥሯል። "እግዚአብሔር መኰንነ ጽድቅ ኃያል ወመስተአግሥ ወኢያመጽእ መንሱት ኩሎ አሚረ - እግዚአብሔር የእውነት ዳኛ ነው ኃይለኛም ተጋሽም ነው፤ ሁል ጊዜም አይቆጣም" እንዲል መዝ ፯÷፲፩ - ፲፪።
- ➢ ውኃ መንጽሒ ነው ሁሉን ያነፃል ጌታም አነ ውእቱ መንጽሔ ሥጋ ወነፍስ ሲል ውኃን ፈጥሯል። "ወነበነ ማየ መንጽሔ ዚአነ" እንዲል አልመስጦአግያ ፪÷፯።
- ➢ መሬት ባዕል ነው ብዕል ሁሉ ይገኝበታል "ወበረከተ ምድር እንተ ባቲ ኩሉ" ብሎ እንዲያመጣው ጌታም ሁሉ የተገኘው ከእርሱ ነውና ባዕል ነኝ ሲል መሬትን ፈጠረ። "ባዕል እግዚአብሔር ከሐሊ እግዚአብሔር" እንዲል ኢዮብ ፲፫÷፫።

፪.፪ የመላእክት ባሕርይ፡- ሙሴ የመላእክትን አፈጣጠር በመጽሐፉ ባይገልጸውም "ወርኢኩ እም ድኅረዝ አእላፈ አእላፋት ወትእልፊተ አእላፋት ወአልቦሙ ኁልቆ ወሐሳበ ለእለ ይቀውሙ ቅድመ እግዚእ መናፍስት" ብሎ ሄኖክ በሄኖክ ፲ ላይ እንደገለጸው የመላእክት ኅልውናቸው የታመነ ነው። በባሕሪያቸውም እሳታውያን ነፋሳውያን ናቸው እንጂ እንደ ሰው ነፍስና ሥጋ የላቸውም። አንዳንድ ሰዎች በመዝ ፻፫÷፬ ላይ "ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈሰ ወለእለ ይትለአክዎ ነደ እሳት" የሚለውን ይዘው እም ግብር ኀበ ግብር ማለት ከነፋስና ከእሳት የተፈጠሩ ናቸው ይላሉ ነገር ግን "ሶበሰ ተፈጥሩ እምነፋስ ወእሳት እሞቱ ወእማሰኑ ከማነ ይላልና ተፈጥሯቸው እም ኀበ አልቦ ነው ተፈጥሮሙሰ ለመላእክት እምብርሃን እምላካዊ እንዲል።" ስለዚህ "ዘይሬስዮሙ ለመላእክቲሁ መንፈሰ ወለእለ ይትለአክዎ ነደ እሳት" ያለው እሳት ነፋስ ኃያላን ረቂቃን ፈጣኖች ፈጻምያነ ፈቃድ ናቸው መላእክትም ኃያላን ረቂቃን ናቸውና ለተልእኮ ይፋጠናሉ የፈጣሪያቸውን ፈቃድ ይፈጽማሉ ሲል ተናገረው።" ተብሎ ተተርጉሟል።

መላእክት የወንድና የሴት ጾታ የላቸውም አይሞቱም አይለወጡም። በዘፍጥረት ፮÷፪ ላይ የተጠቀሰውን በማንሳት ከመላእክት ወገን ዝሙት ሰርተው ምድረ ፋይድ እንደወረዱ የሚናገሩ እንዳሉ አባ መልከጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ ዘካሊፎርኒያ "የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት" በሚለው መጽሐፋቸው ገጽ ፻፵፫ ላይ ይገልጻሉ። በዘፍጥረት ላይ የተገለጸው ግን ስለ ደቂቀ ሴት እንጂ ስለ መላእክት አይደለም። ዮሐንስ በራዕ ፲፬÷፮ እንደገለጸው "ወእምዝ መጽአ ካልእ መልአክ እንዘ ይሠርር ማእከለ ሰማይ ወምድር" እንዳለ ሲገለጡም በክንፍ ታይተዋል ይህም ክንፉ ጸጋ እንጂ አካል ከሌላቸው ክንፍ ሊኖራቸው አይችልም። ታዲያ መላእክት ከየትኛውም አቅጣጫ ቢሆን ሲለምኗቸው ፈጥነው ይደርሳሉ ይህ ማለት ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ምልኡ በኩለሄ ናቸው ማለት አይደለም የመላእት ተፈጥሮአዊ ባሕርያቸው በጣም በጥቂቱ ይህን ይመስላል።

፪.፫. ባሕርየ ሰብእ፡- የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ ባሕርይ (Ontological Neture) በሥሙ ተገልጧል። ሰብእ የሚለው የባሕርይ ሥሙ ሰባትነቱን ያመለክታል ሲጻፍም መነሻ ፊደሉ እሳቱ "ሰ" የሆነው ይህንኑ ሰባትነቱን ለማመልከት ነው። ይህም ከአራት ባሕርያተ ሥጋና ከሦስት ባሕርያተ ነፍስ የተገኘ ነፍስና ሥጋ በተዐቅቦ ተዋሕደው የተፈጠረ ፍጡር ነው። በሌላ በኩል የሰውን ልጅ የተለየ የሚያደርገው በአምሳለ እግዚአብሔር የተፈጠረ መሆኑ ነው። እግዚአብሔር የተጸውዖ ሥሙን "አዳም" ብሎታል ይህ ሥሙ በአምሳለ እግዚአብሔር የተፈጠረ መሆኑን ያመለክታል። "ወአዘዘ እግዚአብሔር ለአዳም" በሚለው የመጽሐፍ አነጋገር ውስጥ የአዳምን የሥሙን ትርጓሜ ስናይ አ፡ፘ፣ ደ፡፪፣ መ፡፬ ፘ+፪+፬ = ፪ፘ፬ "ወያዕቆብኒ ወለደ ዮሴፍሃ ፈታሪሃ ለማርያም እንተ እምኔሃ ተወልደ እግዚእ ኢየሱስ ዘተብህለ ክርስቶስ" ማቴ ፩÷፲፮ በሚለው መንባብ ውስጥ የተጠቀሰውን "ኢየሱስ" የሚለውን ስናይ አ፡ፘ፣ የ፡፯ ሰ፡፭ ሰ፡፭ ፘ+፯+፭+፭ = ፪ፘ፬ ነው። ይህም በሙ ንግበር ሰብእ በእርአያነ ወበአምሳሊነ ያለውን በሐዲስ ኪዳን እራሱ ክርስቶስ እንዲህ ገልጾታል። ስለዚህ የሰው ነገረ ኅልውና በግዘፍነትም በረቂቅነት፣ በመዋቲነትም በሕያውነትም፣ በምድራዊነትም በሰማያዊነትም፣ በሥጋዊነትም በመንፈሳዊነትም፣ በጊዚያዊነትም በዘለዓለማዊነትም፣ የሚገለጽ ነው። "ንለቡ እንከ ከመቦ ውስተ ሥጋነ ነፍስ እንተ ኢትመውት ወኢትማስን ምስለ ሥጋ" እንዳለ ሃይ.አበ. ፮÷፲፱። ታዲያ የሰው ልጅ ኩነተ ኅልውና ይህን የሚመስል መሆኑ ከታወቀ "ኦ አዳም መሬት አንተ ወ ትገብዕ ውስተ መሬት" ብሏል ብለን መሬታዊ ብቻ የማንለው መሆኑን አንድ ይሏል።

ነገር ግን አሁን ባለው ዓለም ውስጥ የሰውን ልጅ ክብር ለማዋረድ የሚሞክር የሰውን ነገረ ኅልውናም ፍጹም በተሳሳተ ዕይታ የሚተነትን የሐሰት ሳይንስ ተፈጥሮ ብዙ የዓለም ሊቃውንትም ተሰልበውበታል። ይህም የዳርዊን የሐሰት ሳይንስ ነው። ይህ ሰው ፲፰፻፹፭ እ.ኤ.አ በታተመውና በተባለው መጽሐፉ "የሰው ልጆችና ጦጣዎች ከአንድ የጋራ ዝርያ የተገኙ ናቸው።" በማለት በኦሪት ዘፍጥረት የተቀመጠውን "እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረው" የሚለውን በመርሳት የተደረገ የሐሰት ጥናት ነው ።

፪.፬. ባሕርያተ ብርሃናት

ይህንንም ሊቁ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ በመጽሐፉ አክሲማሮስ ሲያብራራ "ወእምዝ አሥአ እግዚአብሔር እሳተ ወነፋሰ በበንስቲት ወገብረ ሰሌዳ ፀሐይ ወዓዲ ነሥአ እግዚአብሔር ነፋሰ ወማየ በበንስቲት ወገብረ ሰሌዳ ወርኅ ወሰሌዳ ከዋክብት" አክ.ዘረብዕ ፪-፫ በማለት እግዚአብሔር የፀሐይን ሰሌዳ ከእሳትና ከነፋስ ፈጠረ ይህም ይታወቅ ዘንድ በእሳትነቷ ታተኩሳለች በነፋስነቷ ትሄዳለች፤ የጨረቃና የከዋክብትን ሰሌዳቸውን ከነፋስና ከውኃ ፈጠረ፤ ይህም

ይታወቅ ዘንድ በነፋነታቸው ይሄዳሉ በውኃነታቸው ይቀዘቅዛሉ። በዘፍጥረት ትርጓሜ ላይ አንድም የፀሐይም የጨረቃም ተፈጥሯቸው ከነፋስ ከእሳት ነው እግዚአብሔር ፀሐይን ሙቂ ድመቂ ቢላት ትሞቃለች ትደምቃለች፣ ጨረቃን ድመቂ አትሙቂ ቢላት ትደምቃለች እንጂ አትሞቅም።

"ወእምዝ ነሥአ እግዚአብሔር ብርሃነ እምዘዚአሁ ብርሃን መጠነ ኅጠተ ስርናይ" እንዲል አክ.ዘረቡዕ ፭ እግዚአብሔር የስንዴ ቅንጣት የምታህል ብርሃን ወስዶ ለሰባት ከፍሎ አምስቱን ለፀሐይ ሁለቱን ለጨረቃ ቀባቸው፤ ነገር ግን ፀሐይ ብርሃኑ ኃያል ቢሆን ሦስት እጁን ለፀሐይ አስቀርቶ አንዱን እጅ ለከዋክብት፣ አንዱን እጅ ለማያትና ለደመና ቀባቸው። ፀሐይም፣ ጨረቃም፣ ከዋክብትም ብርሃናቸው አሁን የመናየውን ሆነ። ፀሐይንም በቀን አሠለጠነው ጨረቃንና ከዋክብትንም በሌሊት አሠለጠናቸው።

የብርሃናት ባሕሪያቸውም እግዚአብሔር እርሱ ባወቀ ከቀባቸው የብርሃን ቅንጣት ክፍልፋይ አንጻር ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብት ብርሃንን ይሰጣሉ።

ፀሐይ መዓልትን ስትመግብ ጨረቃና ከዋክብትም በሌሊት እንዲሰለጥኑ ስለተደረጉ መዓልቱንና ሌሊቱን እየመገቡ ዘመን እንዲወለድ ያደርጋሉ። ለምሳሌ በዘመን አቆጣጠር ውስጥ ከዋክብት ከፍተኛ ቦታ አላቸው ለ፲፪ቱ ወራት ፲፪ መገብተ አውራኅ ከዋክብት አሏቸው እነዚህም ደለው፣ ሐት፣ ሐመል፣ ተውር፣ ጀውዝ፣ ሺማን፣ ዐቅራብ፣ ሚዛን፣ ቀውስ እና ሺሺያ ይባላሉ። ለእነዚህ ደግሞ አረእስት የሚሆኑ ዐመቱን ለአራት ተካፍለው አራቱን ወቅቶች የሚመግቡ ህልመልሜሌክ፣ ብርክኤል፣ ምልኤል እና ናርኤል ናቸው። አራቱ አበይት ከዋክብት ይመግቢቸዋል። ይህንም አለቃ ያሬድ ፈንቴ ባሕረ ሐሳብ በተባለ መጽሐፋቸው ገጽ ፴፯ - ፴፯ "ከመጋቢት ፷፯ - ሰኔ ፷፭ ያለው ዕለት ፯፭ ይሆናል። ዘመኑ በእኛ ጸደይ በዕበራውያን መፀው ነው። መጋቢው ኮኩብ ምልክኤል ይባላል መሬትን ይመግባል። ከሰኔ ፷፯ - መስከረም ፷፭ ያለው ዕለት ፯፭ ነው። ዘመኑም በእኛ ክረምት በዕበራውያን ሐጋይ ነው። መጋቢው ኮኩብ ሕልመልሜሌክ ይባላል። ውሃን ይመግባል። ከመስከረም ፷፯ - እስከ ታህሣስ ፷፭ ያለው ዕለት ፯፭ ነው ዘመኑ በእኛ መፀው በዕበራውያን ጸደይ ነው። መጋቢው ኮኩብ ሚላኤል ይባላል ነፋስን ይመግባል። ከታኅሣሥ ፷፯ - መጋቢት ፷፭ ያለው ዕለት ፯፭ ነው። ዘመኑ በእኛ ሐጋይ በዕበራውያን ክረምት ነው። መጋቢው ኮኩብ ናርኤል ይባላል እሳትን ይመግባል።" በማለት እንዳስቀመጡት ከዋክብት ራሳቸው ፀሐይን እየተከተሉ ዑደታቸውን ያደርጋሉ ለዘመናት መለወጥም ምልክት ይሆናሉ። እነዚህ ከዋክብ በሰማዩ ላይ ወተት የተረጨ ወይም ወተት የፈሰሰበት መስሎ ይታያል ብለው የካሊፎረኒያ ሊቀ ጳጳስ አባ መለከ ጴጴቅ እንደገለፁት በሰማይ መካከል መቀነት የመሰለ የከዋክብት ክምችት ይታያል ይህም በግሪክ ቋንቋ ጋላክሲ ይባላል።

፪.፭. የሰባቱ ሰማያት ተፈጥሮአዊ ባሕርይ፦ እነዚህ ሰማያት ሰባትነታቸው በትውፊት የታወቀ እንጂ መጽሐፍ በግልጥ አልዘረዘራቸውም ባሕርያቸውም እንዲሁ በግልጥ የሚታወቅ ባለመሆኑ ለእኛ ለሰው ልጆች የማይታዩ ረቂቃን መንፈሳውያ ዓለማት ናቸው። እነዚህ ሰማያት ግን ብርሃናውያት መሆናቸው ከአባቶቻችን በተገኘ ትውፊት ይገለጣል። ለምሳሌ ኤረር ብሩህ ሰማይ ነው። እርሱም ከጠፈር በላይ የመጀመሪያው ሰማይ ነው። ራማ ሁለተኛው ሰማይ ነው። ኢዮርም መካከለኛ ሰማይ ነው። እነዚህ ሦስቱም ዓለመ መላእክት እንደሆኑ ይታመናል። ሰማያት ብዙ መሆናቸው "ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር" ብሎ ቅዱስ ዳዊት ሲናገር በጸሎተ ሃይማኖት ላይም "ነአምን በአሐዱ አምላክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኩሉ ገባሬ ሰማያት ወምድር" በማለት ተገልጧል። እነዚህ ሰባቱ ሰማያትም

አንዱ ከአንዱ በጣም የተራራቁ መሆናቸውን “እነዚህም በአንድ ላይ የተያያዙ የተገናኙ ሳይሆኑ አንዱ ከሌላው ከፍተኛ ርቀት ያለው ነው ለምሳሌ በዘመናዊው ተሽከርካሪ ከአንደኛው ወደ ሌላኛው ሰማይ ለመሔድ ቢቻል አንድ ሺህ ዓመት እንደሚፈጅ ይነገራል” ብለው “የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ትምህርት” የሚለው መጽሐፍ ደራሲ አባ መልከ ጼዴቅ ሊቀ ጳጳስ ይገልጻሉ። በአጠቃላይ ስለ ሰባቱ ሰማያት ፍጠረታዊ ባሕርይ ከዚህ በላይ ማለት አይቻልም።

፪.፮. ብሔሞትና ሌዋታን፦ እነዚህ ፍጥረታት እግዚአብሔር በዕለተ ሐሙስ ከፈጠራቸው ፍጥረታት መካከል ሲሆኑ ባሕርያቸው ለየት ያለ በመሆኑ በተለየ ሁኔታ ማየት አስፈላጊ ስለሆነ እንደሚከተለው ልንገፃቸው ወደድን። በሔሞት ዝሆን ነው በየብስ ተፍጥሯል። ሌዋታን አሳነባሪ ናት ከባሕር ተፈጥራለች ምን ይመገባሉ ቢሉ ለብሔሞት በየብስ ካሉ ፍጥረታት ከሰው በቀር ሺህ ሺህ በፀጉሩ ይገባለታል ያን እየተመገበ ይኖራል፤ ለሌዋታን በባሕር ካሉ ፍጥረታት ሺህ ሺህ በጸጉሯ ይገባላታል ያንን እየተመገበች ትኖራለች። ኩበሔሞትና ከሌዋታን ጋር ተያይዞ የሚነሳው ዋና ነጥብ እግዚአብሔር ከምድር ከፍሎ ለእነዚህ ፍጥረታት የሰጠው ድርሻ ጉዳይ ነው። ይህም እንዲህ ነው። ምድሩን ዙሪያ ዙሪያውን ለሰባት ከፍሎ አንዱን ክፍል ለብሔሞት ሰጥቶታል የብሔሞትን ዕጣም ከሦስት ከፍሎ በአንዱ እሱን አስተኝቶበታል፤ ሁለቱ ምግብ ይመላለስበታል፤ ሦስተኛውን ዕጣ ለሌዋታን ሰጥቷታል፤ የሌዋታንንም ዕጣ ከሦስት ከፍሎ በአንዱ ክፍል እሷን አስተኝቶበታል፤ በሁለቱ ምግብ ይመላለስበታል፤ በሦስተኛው ዕጣ በድምጽ የሚገድሉ ግሩማን አራዊትን አስፍሮበታል፤ በአምስተኛው ዕጣ እሳት አስፍሮበታል፤ በስድስተኛው ዕጣ በረድ ያጸራበታል፤ ሰባተኛውን ዕጣ ለሰው ሰጥቶታል። ብሔሞትና ሌዋታን እንደ መቀነት፣ እንደ ቀለበት ምድር እንደ ወጉበ፣ እንደ ጣት ዙሪያዋን ተጠምጥመው ይኖራሉ (ሥነ ፍጥረት ዲ/ን ከፊያለው ታደሰ ጎዳር ፲፱፱፱ዓ.ም) ብሎ እንዳብራራው እነዚህ ብሔሞትና ሌዋታን እጅግ በጣም ግዙፋን ፍጥረታት ቢሆኑም ነገር ግን የተሰወሩ ናቸው። ቅዱሳን ሲበቁ የሚያዩዋቸው ግሩማን አራዊተ ምድር ናቸው። በዚህ የተነሳ የሰው ልጅ የብሔሞትና የሌዋታንን ነገረ ጎልውና ተፈጥሮአዊ ባሕርያቸውን ከዚህ በላይ ማወቅና መተንተን አይቻለውም ማለት ነው።

<u>፫. የፍጥረታት ፍጻሜአቸው</u>

የፍጥረታት ፍጻሜአቸውን በሁለት ከፍሎ ማይት የቻላል።

፫.፩. ተሰርተው ስለመፈጸማቸው

፫.፪. ከጎልፈተ ዓለም አንጻር

፫.፩.ተፈጥረው ስለመፈጸማቸው፦ ይህ ማለት ሙሴ በዘፍጥረት “በቀዳሚ ጉበረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ” ብሎ ብሔረ ዖሪትን እንደጀመረ እግዚአብሔርም ፍጥረታትን በመጀመሪያዋ ዕለት በቀዳማይ ሰዓተ መዓልት ሰማይንና ምድርን ከመፍጠር ጀምሮ በስድስተኛው ዕለት በዕለተ ዓርብ በነግሕ እጓለእመሕያ አዳምን ፈጥሮ አጠናቀቀ “ወአዕረፈ እግዚአብሔር በሳብዕት ዕለት እምኩሉ ግብሩ” እንዲል መጽሐፍ በሰባተኛዋ ዕለት ድካም ኖሮበት ሳይሆን ሰንበት ክብርት መሆኗን ለመግለጥ እግዚአብሔር ሥራ ከመስራት አረፈ ተባለ።

ከእሁድ እስከ ዓርብም በአጠቃላይ ብዙው እንደ አንድ ብዙው እንደ አንድ እየተቆጠረ ፷፪ ሥነ ፍጥረታት ተፈጥረዋል። እነዚህም በሃያው ዓለማት እነዲኖሩ አድርጓቸዋል። ሃያው ዓለማት የሚከተሉት ናቸው፡-

- ✓ <u>ዓለመ እሳት</u>

፮. ጽርሐ ዓርያም

፪. መንበረ መንግሥት

፫. ሰማይ ውዱድ

፬. ኢየሩሳሌም ሰማያዊት

፭. ኢዮር

፮. ራማ

፯. ኤረር

፰. ምጽናተ ሰማይ

፱. ገሃነመ እሳት

- ✓ <u>ዓለመ ነፋስ</u>

  ፲. አየር/ነፋስ (ከጠፈር በላይ)

  ፲፩. አየር/ነፋስ (ከበርባሮስ በታች)

- ✓ <u>ዓለመ ማይ</u>

  ፲፪. ሐኖስ

  ፲፫. ጠፈር

  ፲፬. ውቅያኖስ

  ፲፭. ዓለምን የከበባት ውኃ

- ✓ <u>ዓለመ መሬት</u>

  ፲፮. ገነት

  ፲፯. ብሔረ ሕያዋን

  ፲፰. ብሔረ ብፁዓን

  ፲፱. መሬት

  ፳. ሲዖል

እነዚህ ሃያው ዓለማት በአጠቃላይ ፳፪ቱ ሥነ ፍጥረታት የሚኖርባቸው ሲሆኑ ነዋሪዎቹን ከነ መኖሪያቸው አስማምቶ የመደበው ደግሞ የዓለማት አስገኚው ራሱ እግዚአብሔር ነው።

፫.፪. የሥነ ፍጥረት ፍጻሜ ከኅልፈተ ዓለም አንጻር፦ “ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም” ብሎ ራሱ ጌታ እንደተናገረው ከእሱና ከቃሉ በቀር “ዓለሙኒ ኃላፊ ወኩሉ ኃላፊ” እንደተባለ ሁሉም አላፊ ነው። ነገር ግን ከዘመኑ ፍጻሜ ጋር ደግሞ የማያልፉ ዘለዓለማውያት ፍጥረታት እንዳሉ መዘንጋት የለበትም። ለምሳሌ መላዕክት አያልፉም፣ ሰባቱ ሰማያት አያልፉም፣ ገሃነም አታልፍም። ከእነዚህ ውጪ ያሉት ግን ቦታ ቢሆኑ ፍጥረት የማይኖርባቸው ሰው፣ እንስሳትና አራዊት ቢሆኑ ከመጀመሪያ ቦታቸው የማይኖሩ ያሆናሉ። የሰው ልጅ ግን ከዚህ ምድር ወደ ሌሎች ዓለማት ማለትም ወደ መንግሥተ ሰማይ ወይም ወደ ገሃነም ስለሚዛወር ያልፋል ተባለ እንጂ የሰው ልጅማ ከኅልፈተ ዓለም በኋላ በመንግሥተ ሰማያት የሚኖር ከሆነ አኗኗሩ እንደ መላእክት

የማይሞት፣ የማይራቆት፣ የማይራብ፣ የማይጠማ፣ የማያገባ፣ የማይጋባ በሆነ ዘለዓለማዊ ኅልዎት እንደሚኖር የታወቀ ነው። ዅሉንም ከገባም በሞት እገላገለዋለሁ በማይለው መከራ ለዘዓለም ሲሰቃይ ይኖራል ማለት ነው።

ስለ እግዚአብሔር ማንነት እና ባሕርያት።

እግዚአብሔር በፍጥረታት የማይመረመር አምላክ ነው ።

እግዚአብሔር በፍጥረቱ ለፍጥረቱ በቸርነቱ የሚገለጠው እግዚአብሔር ከማንኛውም ሌላ ሁናቴ የተለየና የላቀ በመሆኑ የእርሱን ባሕርይ መግለጽ አይቻልም ከአስተሳሰባችንና ከችሎታችን በላይ ነው ለእግዚአብሔር ምሳሌነት ብቁ የሚሆን ምንም ነገር የለም ኢሳ **40 18** በመለኮታዊ ክብሩ ለዘለዓለም በራሱ የሚኖር ነው በመሆኑም ባሕርዩን መመርመር አይቻልም **1** ቆሮ **13 12** ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ከሚገልጡበት መገለጫዎቹ በጥቂቱ ለማየት ያህል ።

1 መንፈስ ነው እግዚአብሔር ረቂቅ ስለ ሆነ በአእምሮችን አማካኝነት ልናውቀው አንችልም እግዚአብሔር መንፈስ ነው ረቂቅ ነው ሲባል ዝርው ብትን አካል የሌለው ማለት አይደለም ረቂቅ መንፈሳዊ አካል ያለው ነው ለግዙፍ አካል መስፈርት የሚሆኑ እንደመጠን ትልቅነት ክብደት የመሳሰሉት ለእግዚአብሔር አይሆኑም ረቂቅ አምላክ ነውና የሐ ሥ **4 24 2** ቆሮ **3 17** ከውሃ አሳት ይረቃል ከአሳት ነፋስ ይረቃል ከነፋስ መላእክት ይረቃሉ ከመላእክት ሓሳባቸው ይረቃል እግዚአብሔር ከመላእክት ከሐሳባቸውም ይረቃል የመላእክት ሓሳብ በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ተራራ የገዘፈ ነው ።

2 ዘለዓለማዊ ነው

እግዚአብሔር በዘመናት የማይቆጠር መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘለዓለማዊ ነው የጊዜና የዘመናት ፈጣሪ ሉቃ **1**፡ **37** ለዘመኑም ጥንትና ፍጻሜ የለውም መዝ **89 /2** መዝ **101 24** መዝ **144 13** ኢሳ **44 6** ራዕ **1 8**

3 ሁሉን ቻይ እግዘአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ ነው የሚሳነውም የለም ዘፍ **18 14** መዝ **134 6** ኤር **32 17** ማቴ **19 26** ሉቃ **1 37**

4 አይለወጥም

እግዚአብሔር በውሳኔው የሚጸና ያለውን የሚያደርግ የተናገረውን የሚፈጽም በውሳኔው እንደሰው የማይጸጸት አምላክ ነው ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ ጻድቅ የባሕርይ አምላክ ነው ተወዳዳሪ የሌለው ፍጹም በመሆኑ ከዚያ የበለጠ ፍጹምነት ሊኖር ስለማይችል የበለጠ ፍጹም በመሆኑ አይለወጥም አሁን ካለው ደግነት መሓሪነት ትክክለኛ ፍርድ ፈራጅነት ቅዱስነት አዋቂነት ብርታት ኃያልነት አይቸምርም አይቀንስም ፍርዱም በጊዜና በሰዓት ያልተወሰነ በመሆኑ ሓሳቡን መለወጥና ውሳኔውን ማሻሻል አያስፈልገውም ኢሳ **38** ዮና **10** ላይ እግዚአብሔር ከፈረደባቸውና ከጠቆጣ ወዲያ ይቅር አላቸው ይላል ይህ እንዴት ነው ይባል ይሆናል ይህ የተለወተው እግዚአብሔር ሳይሆን ሰዎቹ ናቸው ሰዎቹ ንስሓ በገቡ ጊዜ ከትፋት ድነዋል እግዚአብሔር የማይለወጥና የማይጸጸት መሆኑን የሚያረጋግጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል ዘኁ **23 19 1** ሳሙ **15 29** ሚል **3 6** ሮሜ **11 29**

5 በሁሉ ሙሉ /ምሉዕ በኩሉ/ነው እግዚአብሄር በሁሉ ምሉዕ ነው ከዚህ አለ ከዚህ የለም ወይም ከዚያ አለ ከዚህ የለም አይባልም በሰማይ ይኖራልመባሉም ስለ ክብሩና ስለ ልዕልናው ነው ኤር **23 23 24** መዝ **138 5 10** መዝ **77 18 -21** መዝ **2- 4** ማቴ **5 34** ዮሐ **3 13** ለመለኮት ወርድና ቁመት ላይና ታች ቀኝና ግራ ያለው አይደለም በሁሉ የሞላ ነው እንጅ ለመለኮት በላይ ጠፈር በታችም መሠረት ኖለው አይደለም ግዛቱ በሁሉ የመላ ነው ለመለኮት የሚዘረጋበት የሚሰበሰብበት ያለው አይደለም ጠፈሩ እርሱ መሠረቱም እርሱ ነው እንጂ እንዳለ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም

6 ሁሉን አዋቂ ነው

እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ ነው ከእርሱ የተሰወረ ነገር የልም ያለፈውንና ያሁኑን ያሁኑን የሚመጣውን ያልተነገሩትን ሓሳቦችንና ቃላቶችን ተግባራትን ከመሆናቸው አስቀድሞ ያውቃል መዝ **11 33** ዕብ **4 13** መዝ **138 1** ማቴ **15 13** የሐ **2 23**

7 ቅዱስ ነው

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው በሥራው ሁሉ ክፋትና ርኩሰት የለበትም ንጹህና ፍጹም ደግ ነው እውነተኛ ፈራጅ ምሕረቱ የበዛ ታጋሽ ከቁጣ የዘገየ ፍጥሩንም የሚወድ ጸጋውን ያጎናጸፈነው እርሱ በባህርዩ ቅዱስ እንደሆነ ፍጥረታቱንም

ቅዱሳን እንዲሆኑ ይፈልጋል ዘጸ **15 11** ዘሌ **11 44 19 1** ሳሙ **2 1** ጴጥ **1 13 - 16** ኢሳ **63** ራዕ **4 8** ኢሳ **40 25** ሉቃ **1 48 49**

8 ቸር ነው

እግዚአብሔር ፍቅሩ ርህራሄው ትክክለኛ ፍርዱ ጸጋውና እንዲሁም ለፍጥረቱ የሚያደርገው ጥበቃው ነው ይህን ዓለም ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ የፈጠረው ከደግነቱ የተነሳ ነው በተለይ የሰውን ልጅ በአርአያውና በአምሳሉ ፈጥሮ ፍጹም ነጻነት ያላት ለባዊት ነባቢት ህያዊት ነፍስን በመስጠት ጸጋውን አደለው ዳግመኛም የሰው ልጅ የወደቀበትን የሞት የእርግማን በልጁ ቤዛነት አስወግዶ ዮደፈውን ባሕርዩን ማደሱ ደግነቱን ያጠይቃል መዝ **30 19** መዝ **33 18 144 9 -31** ጢሞ **2 4 2** ኛ ጴጥ **3** ፤**9** መዝ **34** ፣**10**

9 ረዳት አያስፈልገውም

እግዚአብሔር አምላክ የማንም ረዳትነትናድጋፍ የማያስፈልገው ሲሆን በፍጥረት መካከል ግን ያለእርሱ ጠባቂነት ለመኖር ወይም የተፈጥሮ እንቅስቃሴውን ለማድረግ ለማከናውን የሚችን የለም በሁሉም ቻይና በጥበቡ አማካኝነት ፍጥረቱን ሁሉ እንቅስቃሴውንም ሥርዓት አስይዞ የሚዮኖርአምላክ ነው ያለ እርሱ ጠባቂነትና አንቀሳቃሽነት ዐለም ከመኖር ወደአለመኖር ተዛውራ እንዳልነበረች ትሆናለች ሮሜ **11 14** ኢሳ **40 13**

ሰው ምንድን ነው ?

በዓለም አብያተ ክርስቲያናት የትምህርተ መለኮት ጥናት ውስጥ የሚየጠቁ ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎች አሉ። እነዚህ ጥያቄች ዛሬ በምሥራቅ እና ምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ላለው የነገረ ድኅነት ትምህርት ልዩነት መነሻ ሁነው ቀጥለው ይታያሉ። የመጀመሪያ ጥያቄ ሰው ምንድ ነው? የሚለው ሲሆን፤ሁለተኛው ደግሞ የሕይወት ጥቅሙምንድን ነው? የሚል ነው። ሁለተኛውን ጥያቄ በቦታው የምናነሳው ስለሆነ ለጊዜው እናቆየውና የመጀመሪያውን ጥያቄ በቅዱሳት መጽሐፍትና በአበው ትምህርት አስረጅነት እንመልከት።

1 ነቢዩ ዳዊት

ለዚህ ጥያቄ ኦርቶዶክሳዊ ምላሽ ለመስጠት ጥያቄውን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ጠይቆ መልስ ያገኘው ልበ አምላክ ዳዊትን እናስቀድም። “ምንት ውእቱ ሰብእ ከመትዘክሮ” ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጎበኘው ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?” እያለ ይጠይቃል ሲመልስም “ከመላዕክት እጅግ በጥቂት አሳነስኸው ፤በክብር እና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው ፤በእጆችህም ሥራ ላይ ሾምከው ፤ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት” (መዝ 8÷4) በማለት ይናገራል። ስለዚህ የሰው ልጅ ምንነት በምስጋና ያጌጠ በጥንተ ተፈጥሮ ከመላእክት ያነሰ ቢሆንም መላእክትን የመምሰል ምሉዕ ጸጋ የተቸረው፣ መላእክት ግን ያገለግሉትና ይራዱት ዘንድ ለእርሱ የተዘጋጁለት ፤የእግዚአብሔር የእጁ ሥራ በምድራዊያን ፍጥረታት ላይ የጸጋ ገዥነት ሥልጣን ተሰጥቶት የተሾመ ክቡር ፍጥረት ነው። ስለዚህ የሰው ምንነትና ክብር የሚጀምረው ከጥንተ ተፈጥሮውና ከተሰጠው የገዥነት ሥልጣን ነው።

ይህን ክብሩን ጠብቆ ባለመኖሩ ምክንያት የደረሰበትን ፍዳ ሲናገር ደግሞ “ሰብእሰ እንዘ ክቡር ውእቱ ወኢአእምረ ወኮነ ከመ እንስሳ ዘአልቦ ልብ፤ “ሰውስ ክቡር ሁኖ ተፈጥሮ ነበር ፤አላወቀም እንጂ ፤ልብ እንደሌላቸው እንስሳትን መሰለ” (መዝ 49÷15) በማለት ይገልጣል። ስለሆነም የሰው ልጅ በክብር አምላኩን እያመሠገነ በቅድስና በክብር በምሥጋና ኖሮ መንግሥቱን ለመውረስ እንጂ ለምድረ ፋይድ አልተፈጠረም ነበር። በአጭሩ ሰው በመልኩ የእግዚአብሔር አርአያ ሲባል በነፍሱ ደግሞ አምሳለ እግዚአብሔር ይባላል።

ስለሆነም ይህ እግዚብሔርን መመስል መነሻው/መሠረቱ/ ደግሞ የሰው ጥንተ ተፈጥሮ መሆኑ ይታወቃል። የሰው ጥንተ ተፈጥሮ ስንልም በእግዚአብሔር አርአያ እና አምሳል መፈጠሩ (ዘፍ 1÷26)“ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ” የሚለው አምላካዊ ትእዛዝ ነው።

ሰው በጸጋ እንደ አምላክ ይሆን ዘንድ የተዘጋጀ ክቡር ፍጥረት ነው በቅዱሳት መጽሐፍትም ትምህርት ብሉያት እና ሐዲሳት ተባብረው የሚመሠክሩት ቃል ቢኖር ይህ ነው። ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ስለሆነ መነሻውም መድረሻውም እግዚአብሔርን መምሰል ነው ።

ሰውማለትነፋሳዊነት፣እሳታዊነት፣ውኃዊነት፣መሬታዊነትባሕርያትያሉትበነፍስተፈጥሮውምነባቢትለባዊት ናሕያዊትየሆነችነፍስያለችውፍጥረትነው።እንዲህበለን ብቻግንየሰውንተፈጥሮጠቅልለንመናገርአይቻለንም። ምክንያቱምሰውንከሌሎችፍጥረታትይልቅእጅግልዩበሆነሁኔታበእግዚአብሔርአርአያናአምሳልተፈጥሮአልና።

መልኩ

ሰው መልክአሥላሴን የሚመስለውበምንድንነው ?

መልክእ ማለት ከእግር ጥፍር እስከ ራስ ጸጉር ድረስ ያለው መልክአ ገጽ ማለት ነው። መልክእ ሲባል ሥላሴ የሰው ዓይነት የሚታይ የሚዳሰስ ግዙፍ አካላዊ መልክእ አላቸው ማለት አይደለም። ለምን ቢባል በመጽሐፍ “ቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ ነው” (ዮሐ 4÷24) ተብሎ ተጽፎአልና። ስለዚህ የገዘፈ አካል ባይኖራቸውም በሰው ላይ ያለው መልክእ ግን በረቂቅ መንገድ አላቸው።

“እነሆ የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ሚፈሩት ናቸው በምሕረቱም ወደሚታመኑ” (መዝ 32÷18)፤ “የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን ጆሮዎቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸውና”፤ (መዝ 33÷15) “ያዕቆብ ሆይ የጠራሁህም እስራኤል ሆይ ስማኝ እኔ ነኝ፣ እኔ ፈተኛው ነኝ እኔም ኃለኛው ነኝ፤ እጄም ምድርን መሥርታለች ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች”፤ “እነሆ የእግዚአብሔር እጅ ከማዳን አላጠረችም፣ ጆሮውም ከመስማት አልደነቀረችም”(ኢሳ 59÷1) እያለ እንደተናገረው።
አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ምሥጋናው “እግዚአብሔር በሰማይ ሆኖ ተመለከተ ሰማይንና ምድርን ምሥራቅንና ምዕራብን ሰሜንንና ደቡብን ...አሻተተ እንደአንቺ ያለ አላገኘምና” ብሏል። ስለዚህ የሰው ልጅ ሥላሴን በመልክ ይመስላቸዋል ማለት ነው።

1. በአንድነትና በሥስትነት

የአዳም (የሰው ልጅ) ነፍስ አንድ ስትሆን ሦስት ግብራት አሏት እነርሱም ለባዊት፣ ሕያዊት እና ነባቢት ናቸው። ነፍስ አንድ ትባል እንጂ ሦስት አትባልም። ሥላሴም በአብ ልብነት ቢያስቡ ፣በወልድ ቃልነት ቢናገሩ እና በመንፈስ ቅዱስ እስትፋስነት ሕያዋን ሆነው ቢኖሩ አንድ አምላክ ይባላሉ እንጂ ሦስት አማልክት አይባሉም።

2. በሕያውነት

እግዚአብሔር ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ሕያው ነው፤ አዳማዊው የሰው ልጅም የማትሞት ሕያው የሆነች ነፍስ አለችው፤ በሥጋው እንኳን ቢሞት ፈርሶ በስብሶ መቅረት የለበትም፣ በትንሣኤ ሙታን በመነሣት ሕያው ሆኖ ይኖራል እንጂ።

3. በገዥነት

ሥላሴ የዓለማት የፍጥረታት ፈጣሪ ገዢ አስተዳዳሪ ናቸው ሁሉንም ይገዛሉ፤ ሁሉን ያስተዳድራሉ። አዳምም በምድር ላይ ሁሉን ይገዛ ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይህ ጸጋ ተሰጥቶታል።

“እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር፤ የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ” (ዘፍ 1÷26) እንዲል።

እግዚአብሔር አምላክ አዳምን በእርሱ ምሳሌና አርአያ ከሌሎች ፍጥረታት አክብሮ ፈጥሮታል። ሌላው እዚህ ላይ የምንመለከተው ነገር ቀደም ሲል የፈጠራቸውን ፈጥረታት በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት በጨለማው ሲፈጥራቸው አዳምን ግን በነግህ በጠዋት በብርሃኑ ፈጠሮታል፤ ይህም ሠርክ (ማታ) ጨለማ ይከተለዋል ወይንም በጨለማ ይሸፈናል እንስሳትም አራዊትም አዕዋፍም ጽሉማነ አእምሮ (ዕውቀት የሌላቸው) በደመ ነፍሳዊ የሚንቀሳቀሱ ናቸው ሲል ነው።

እንዲሁም መዋትያን (የሚሞቱ)፣ ፈርሰው በስብሰው፣ ነፍሳቸው በና ተንና የምትጠፋ ስለሆነ፤ በምድር በስብሳችሁ ፈርሳችሁ የምትቀሩ ናችሁ የሚለውን ለማስረዳት በሌሊት እነርሱን ፈጠረ።

ነግህ ብርሃን ይከተለዋል አዳምን ብሩህ አእምሮ ያለህ ነህና፣ በሃይማኖት በምግባር ብትገኝ ብሩህ መንግሥተ ሰማያት ትጠብቅሃለች ሲለው ነው። ሥላሴ አዳምን ሲፈጥሩት ድካም፣ እንቅልፍ፣ መንቃት፣ የሚስማማው አድርገው ነው። ይህም ድካምና እንቅልፍ የሥጋ፤ መንቃትና መትጋት የነፍስ ግብር መሆኑን ያሳውቃል።

ሌሎቹን ፍጥረታት እንስሳት፣ አራዊትና አዕዋፍን አስጎንብሶ አዳምን ግን አቅንቶ ፈጥሮታል፤ ይህም አዳም የገዢ እነርሱ ደግሞ የተገዢ፤ አንድም አዳም ትንሣኤ ያለው እናንተ (ሌሎቹን ፍጥረታት) ግን የላችሁም ሲል ነው።

የእግዚአብሔርን መንገድ የተከተለ ሰው (መንፈሳዊነት)

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን በአርአያውና በአምሳሉ መፍጠሩ ሰውን ከሥነ - ፍጥረት ሁሉ ለይቶ እንዳከበረውና እንደወደደው ያስረዳል። ዳግመኛም ከጥንተ ተፈጥሮ በበለጠ አኳኋን በሐዲስ ተፈጥሮ ሰውን እግዚአብሔር ምን ያህል እንደወደደው በልጁ በፈፀመው የማዳን ሥራ በተጨባጭ ተገልጿል ። በዚህም የሰው ልጆች ሁሉ በክርስቶስ አምነው በመጠመቅ በክርስትና ሕይወት እንዲኖሩ ተጠርተዋል፤ በክርስትና ሕይወት የ ሚኖር ደግሞ ክርስቶስን መምሰል ይጠበቅበታል። ክርስቶስን መምሰል በማሰብ ብቻ ሳይሆን በተግባርና በሚገለጥ ማንነት መታየት ነው። በመሆኑም በክርስቶስ ክርስቲያን የተባለ መንፈሳዊ ሰው በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድና ኀይል ሕይወቱን የሚመራ ከሚታየው ዓለም ፈቃድ ራሱን ያራቀ ነው። በሕይወቱም የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ የሚነበብበትና በእግዚአብሔር ፈቃድ የሚመላለስ ነው። መንፈሳዊነት ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ አንዱና ዋነኛው የሕይወት መንገድ ነው፤ ይኸውም ከሥጋ ሃሣብ በመለየት ለሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስነት በመንፈስ ቅዱስ መታነጽ ነው።

1. የመንፈሳዊነትና መንፈሳዊ ሕይወት ትርጉምና ጽንሰ ሃሳብ

መንፈስ ማለት የማይመረመር የማይዳሰስ የማይጨበጥ በዓይነ ሥጋ የማይታይና ረቂቅ አካል ያለው የማይወሰን ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ "መንፈስ" የሚለው ቃል ብዙ ትርጉም ተሠጥቶት እናገኘዋለን፤ በዚህም መንፈስ የሚለው ቃል በቅጽል ካልተገለጠ በቀር የተለያየ ትርጉም ይኖረዋል። በግልጽ ከታወቁት ምንባቦች በቀር መጽሐፍ ቅዱስን በምናነብበት ጊዜ በአንዳንድ ቦታ ያለ ቅጽል መንፈስ የሚለውን ስናገኝ የእግዚአብሔር መንፈስ ወይም የሰው መንፈስ ወይም ሌላ ዓይነት መንፈስ እንደሆነ የምናውቀው በዐረፍተ ነገሩ አገባብ ወይም በአንቀጹ ይዘትና ሁኔታ ነው። ነገር ግን መንፈሳዊነት ወይም መንፈሳዊ ሰው ስንል ከሥላሴ ልጅነትን ካገኘ በኋላ በምግባር በትሩፋት በመግለጽ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ሕግ የሚጓዝ ማለት ነው።

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ረቂቅ የማይዳሰስ፣ የማይጨበጥ፣ የማይወሰን፣ የባሕርይ አምላክ ነው። መዝ 139፡7 እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ለምዕመናን በጥምቀት የማይታየውን ዘላለማዊ የልጅነት ጸጋ ይሰጣል። ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት መንፈስ ተቀበላችሁ እንጅ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን መንፈስ አልተቀባችሁም´ ሮሜ 8፡15 በማለት ክርስቲያኖች ሁሉ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የልጅነት ጸጋ እንደተሰጠን የሚያስረዳ እንዲሁም ለቆሮንቶስ ምዕመናን በላከው መልእክቱ "የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደሆናችሁ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን" 1 ቆሮ 3፡16-17 በማለት በወልድ ውሉድ እንደተባልን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ደግሞ መንፈሳውያን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ እንደተባልን ያስረዳናል። ስለዚህ ሰው መንፈሳዊ የሚባለው የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የሆነውን ሰውነቱን ከኀጢአት ጠብቆ ፈቃደ እግዚአብሔርን ሲፈጽም ብቻ ነው።

<u>መንፈሳዊ ሕይወት</u>

መንፈሳዊ ሕይወት ስንል መንፈሳዊ ኑሮ፣ ክርስቲያናዊ አኗኗር ለማለት ሲሆን በቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ የተቃኘ ኑሮ ማለት ነው። በዚህም መንፈሳዊ ሕይወት ፈቃደ ሥጋን ለፈቃደ ነፍስ የሚያስገዙበት አኗኗር ነው። ፈቃደ ሥጋ ወይም የሥጋ ፍላጎት ፈጽመው ቢከተሉት ከእግዚአብሔር ሊያርቅ፣ ከሕግ ከሥርዓት ሊያናውጽ የሚችል ነው። ፈቃደ ሥጋ ለጊዜው ብቻ ይድላኝ፣ ይመቸኝ፣ የሚያሰኝ ሲሆን የወደፊቱንና ዘላለማዊውን የማያገናዝብ ነው። ፈቃደ ሥጋ ሙሉ በሙሉ ሰውነትን ሲቆጣጠር፣ ጎሊናን ሲይዝ ከእግዚአብሔር ያርቃል ።

አንድ ክርስቲያን ልዩ ልዩ የሥጋ ፍላጎቶችን ለነፍስ ፍላጎቶች ሲያስገዛ ይህን አኗኗር መንፈሳዊ ሕይወት እንለዋለን።

የሰው ልጅ እንስሳዊና መልዓካዊ ጠባያት አሉት። ሙበላት፣ መጠጣት፣ መተኛት፣ ማንቀላፋት፣ መዋለድ... የመሳሳሉት በእንስሳዊ ጠባይ የሚካተቱ ሲሆኑ መጾም መጸለይ፣ መቀደስ፣ መዘመር... የመሳሰሉት ደግሞ

በመልዓካዊ ጠባዩ የሚታሰቡ ናቸው። አንድ ክርስቲያን ለሥጋዊ ፈቃዱ በመገዛት ለጊዜው የሚያስደስቱ፣ ስሜትን የሚከተሉትንና ለሥጋ ብቻ የሚደሉትን ሲከተል እንዲኖር አይገባም። በቀል፣ ራስ ወዳድነትን፣ ውዳሴ ከንቱን የመሳሰሉትን ሀሳቦች አሸንፎ ራስን ለነፍስ ፈቃድ አስገዝቶ መኖር መንፈሳዊ ሕይወት ነው።

መንፈሳዊ ሕይወት ክርስቶሳዊነት ነው። ለስም አጠራሩ ክብር ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋን ተዋህዶ ወደዚህች ዓለም ከመጣበት ዓላማዎች አንዱ አርአያነት ነው። በባሕርይው ንጹህ የሆነው አምላክ ሳይበድል ካሳን ፈጽሟል። ፍጹም የትህትናን፣ የፍቅርን፣ የትዕግስትን ሥራ ፈጽሟል። እርሱን ተከትለን ለምንኖር ክርስቲያኖችንም የርሱ ወዳጆች መሆናችንን የምናሳይበትን ‹‹እንዲሁ አድርጉ›› በሚል አርአያነት አሳይቶናል። ሠርቶ፣ ባርኮ አሳየን። ክርስቲያናዊ ኑሮ/መንፈሳዊ ሕይወት/ ክርስቶሳዊነት ነው ሲባል ሳንበድል ብንከሰስ፣ ክፉ ስም ያለ ሥራችን ቢሠጠን... ይህንን ሁሉ ችሎ ማለፍን ነው። የወንድም የእህትን በደል ወይም ገመና መሸፈን ነው። ከባቱ አበሳ የተባለው መድኃኒታችን እኛም የሌላውን ጎጢዓት በጸሎትና በትእግስት ከልብ በመነጨ ፍቅር እንድንሸፍን ይፈልጋል። ያኔ እኛ ክርስቶሳውያን ስንባል ሕይወቱም ክርስቶሳዊነት ይሰኛል።

መንፈሳዊ ሕይወት በውስጥና በውጪ የሚገለጥ ሕይወት ነው። መንፈሳዊ ሰው ማለት ለዕለት እንቅስቃሴው ሁሉ ራሱን /ሕይወቱን/ ለእግዚአብሔር የሰጠ ማለት ነው። በክርስቶስ ተለውጦ አዲስ ፍጥረት የሆነ ማለት ነው። በመሆኑም በልቡናው የመንፈስ ፍሬዎች የውሃት፣ ፍቅር፣ ትህትና፣ በጎነት፣ የተሞላ ሲሆን በውጫዊው /አፍኣዊ/ ሕይወቱም እንዲሁ ይገለጣል።

መንፈሳዊ ሕይወቱ የተለወጠ ሰው በአነጋገሩና በእንቅስቃሴው ሁሉ ለሌላው መድኃኒት ሕይወት፣ ፈውስ ነው። በአለባበሱ፣ በማኅበራዊ ኑሮው ሁሉ የውስጡ ነፀብራቅ ይታይበታል። በምግባር የሚታይ ፍሬ ሃይማኖቱ፣ ፍሬ ምግባሩና ፍሬ ትሩፋቱ በጎላና በተረዳ ነገር የሚታወቅ ይህም ሌላው በመዓዛው ወደ ክርስቶስ የሚስብ ነው።

ሰውነቱን ድንኳን፣ ልቡናውን ዙፋን አድርጎ የሚኖር ባለቤቱና ፈጣሪው እግዚአብሔር ስለሆነ ሃሳቡ፣ ንግግሩም ሆነ ድርጊቱ የተቀደሰ ይሆንለታል። የሚሠራውም ሥራ የሚከናወንለት፣ ውጤቱም የሚሰምርለትና የሚያምርለት ይሆናል።

መንፈሳዊ ሕይወት በቦታና በጊዜ በልዩ ልዩ ሁኔታዎች አይወሰንም። በምድር የሚጀመር ኋላም በሰማይ የሚቀጥል ዘላለማዊ ኑሮ ነው። ስለዚህ በሥራ ቦታ፣ በመንገድ፣ በየትኛውም ሥፍራ ሲተኙና ሲነሱ፣ በቀንና በሌሊት የሚኖሩት ሕይወት ነው። በመሆኑም በማንኛውም ተግባረዕድ ለዕለት እንጀራ በተሰማሩበት ጎላፊነት ሁሉ ማንም ቢያሠራቸው ያንን ተግባር በእግዚአብሔር ከተወጡት ይህ መንፈሳዊነት ነው። ቢተኙ ገላልጦ የሚያይ እግዚአብሔር አለብሎ ሥራውን አሠሪውን አሊያም ሌላ ምስጋና ሳይሻ የሚሠራ ሰው መንፈሳዊ ነው።

2. የእግዚአብሔርን መንገድ የተከተለ ሰው መገለጫዎች

እግዚአብሔርን እከተላለሁ የሚል ሰው በታይታ የማይወሰን፣መሆኑን መረዳት አለበት ። ባለቤቱ መንፈስ ቅዱስ በወደደው ይገለጣልና የፈለገውን ፈቃዱን ያስፈጽመዋል። ወደ መንፈሳዊነት በሚደረገው ጉዞ ውስጥም ሥጋና ነፍስ የሚከፍቱት ጦርነት እጅግ ታላቅ ሲሆን ይህን ውጊያ ነፍስ በአሸናፊነት በመወጣት በሥጋ ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሕግ ተፈፃሚ ባደረገች ጊዜ ይከናወናል እንጂ ስለመንፈሳዊ ሕይወት እውቀትና ግንዛቤ ስላለን መንፈሳውያን ሊያሰኘን አይችልም። በመሆኑም ከመንፈሳዊ ሰው የሚጠበቁ እና የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መገለጫዎችን ቅዱሳት መጻሕፍት የተናገሩትን፣ አበው ያስተማሩትን፣ በፍሬያቸው የተገለጡትን ቅዱሳንን አርአያ በማድረግ የሚከተሉትን ነጥቦች እናስተውላለን።

ሀ/ ለሰማያዊ ዋጋ የሚጋደል

የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር እየሰማ ትዕዛዛቱን እየፈፀመ የሚጓዝ ክርስቲያን ከዓለማዊነት ይልቅ መንፈሳዊነት ይበልጥበታል፤ ለዚህም ዘወትር ተጋድሎውና ጥረቱ ሰማያዊውን ዋጋ ለማግኘት ነው። የዚህም ዓለም ነገር አላፊ ጠፊ መሆኑን በደንብ ስለሚረዳ መንፈሳዊ ሰው ዓለምን ይገዛታል፣ ይሰለጥንባታል አልፎም ተርፎ ንቆ ይተዋታል እንጂ ለጊዜያዊ ደስታ ብሎ መንፈሳዊነቱን በመዘንጋት ለፈቃዱ አይገዛም። ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ እንደፃፈው “ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ፤ ከግብጽ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንደሆነ አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቷልና” ዕብ 11፡23-28 በማለት ሙሴ የሰማያዊውን ዋጋ ታላቅነት በመረዳት የፈርዓንን ቤተ መንግሥት እንደናቀ መስክሮለታል። እንዲሁም ወደ ቆሮንቶስ በጻፈው መልእክቱ “በእሽቅድምድም ሥፍራ የሚሮጡት ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ የሚታገል ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፤ እኛ ግን የማይጠፋውን´ 1 ቆሮ 9፡2 24-27 በማለት መንፈሳዊ ሕይወት ሰማያዊ ሽልማት አክሊል የሚያሰጥ ስለሆነ በጽድቅ ጎዳና ላይ መሮጥ እንዳለብን ያስረዳናል። ስለዚህ በመንፈሳዊ ጉዞ የሚራመድ ክርስቲያን ሁሉ ከፊቱ የተዘጋጀለትን ታላቅ ክብር ትኩር ብሎ በመመልከት ከኃጢአት ተለይቶ የእግዚአብሔርን መንገድ ተመልክቶ በነገር ሁሉ ራስን በመግዛት መንፈሳዊ እውቀትን ወደ መልካም ሥራ በመለወጥ የሚጋደልና የመንፈስ ቅዱስን ፈቃድ ሁሉ የሚፈጽም ነው።

ለ/ሆኖ የሚገኝ

መንፈሳዊነት መስሎ ሳይሆን ሆኖ መገኘት ነው። መንፈሳዊነት በሚመስል ንግግር፣ አለባበስ የሚገለጽ ሳይሆን በተግባር በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ መንፈሳዊ ሕይወት ነው። ቅዱስ ያዕቆብ “ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ። ቃሉን የሚሰማ የማያደርገው ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስታወት የሚያይን ሰው ይመስላል ራሱን አይቶ ይሄዳልና ወዲያውም እንደምን እንደሆነ ይረሳል” ያዕ 1፡ 22-25 እንዳለ ክርስቲያን መንፈሳዊነቱ በማስመሰል ሳይሆን በሥራው የተገለጠ ነው። በዚህም የመንፈሳዊ ሰው ሕይወቱ በእምነት ዓለትነት ላይ የጠነከረ ጣሪያና ግድግዳው ደግሞ በሥራና በምግባር የተገነባ ቤት ነው።

መንፈሳዊ ነኝ እያሉ ከጽድቅ ሥራ ባዶ መሆን እንደፈሪሳውያን በማይጠቅምና በማያድን ሕይወት ውስጥ ጊዜ ማሳለፍና ከንቱ የልማድ ሕይወት ይሆናል። ጌታችንም የአብርሃም ዘር ነን በማለት ሲመፃደቁና በግብዝነት ሲመላለሱ የነበሩትን ጸሐፍት ፈሪሳውያንን “የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር” ዮሐ 8፡39 በማለት ገስጿቸዋል። እንዲሁም ጌታችን መንፈሳዊ ሕይወታችን በጽድቅ ሥራ ላይ እንዲመሠረት ሲያስተምር

“... በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም...” ሲል ማቴ 7፡21-27 ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ “በእግዚአብሔር ፊት ሕግ የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና” ሮሜ 2፡13 በማለት አስተምሯል። ስለዚህ የመንፈሳዊ ሰው ሕይወቱ በማስመሰል ላይ ሳይሆን መልካም ሥራ በመስራት ታምኖ የሚገኝና የእግዚአብሔርን ፈቃድ በማድረግ በዓለት ላይ የተመሠረተ ነው።

ሐ/ ከሚወደው ኃጢአት የተለየ

በኃጢአት የሚኖር ሁሉ የኀጢአት አገልጋይ ነው፤ የኀጢአት ባርያ ደግሞ ከጽድቅ መንገድ የራቀ ነው። ኀጢአተኛ የሚያሰኘው በብዙ ወይም በሁሉም ኀጢአት መውደቅ ብቻ አይደለም አንድም ኀጢአት ቢሆን ከፈጣሪው ስለሚያጣላው ኀጢአተኛ መሆኑ አይቀርም። ኀጢአት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሰናክል ታላቅ እንቅፋት በመሆኑ መንፈሳዊ ሰው ኀጢአት የሆነውን ሁሉ ከመስራትና ኀጢአትንም ከመውደድ መለየት አለበት፤ ሰው የሚወደውን ኀጢአት የተቃቃመ እንደሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ባለድልና አሸናፊ ይሆናል። ኀጢአትን መቃቃም አሸናፊ የሚያደርግ ከሆነ ብዙውን ኀጢአት ተቃቁሞ በአንዱ መውደቅ ረብ የሌለውና የማይጠቅም ስለሆነ መንፈሳዊ ሰው በኀጢአት ሁሉ ላይ አሸናፊነትን ለመቀዳጀት የሚጥር ነው። ለዚህም በመንፈሳዊነት ለመኖር ከኀጢአት የሚለይና በኀጢአት የነበረበትን ዘመን በንስሓ ያስወገደ የአህዛብን ፈቃድ ያደረገበትን ዲያብሎስ በሕይወቱ በምኞቱ የገነባውን የኀጢአት ግንብ በንስሐ ያፈረሰ ነው። ከሚወዱት ኀጢአት ሳይለዩ በንስሓ በር ሳይገቡ በክርስትናው ሕይወት መኖር በእግረ ሥጋ በእግረ ልቡና መመላለስ ባዶነት ስለሆነ መንፈሳዊ ሰው የሕይወት ዘመኑ በሙሉ በንስሓ የተሞላ ታሪኩ ከንስሓ ያልተለየ ማንነት ያለው ነው።

መ/ ፍቅር

በክርስትና ሃይማኖት ፍቅር ከፍተኛ ቦታ አለው። ሃይማኖቱም ምግባሩም በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ የተመሠረተ ነው። ደኅንነትን ያገኘነው እስከ ሞት ድረስ በወደደን በክርስቶስ ፍቅር ነው። በመሆኑም የመንፈሳዊ ሕይወት መሠረቱ በእግዚአብሔር ላይ ያለን ጽኑ ፍቅር ነው መንፈሳዊን ሰው ዓለምን እንዲጠላ ያደረገው በአቅም ዝቅተኛ ኑሮ በመኖሩ፣ ጤንነቱ ባለመሟላቱ ከቤተሰብና ከማኅበረሰቡ ገለልተኛ በመሆኑና በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች ሳይሆን በውስጡ ባለው የእምላኩ ጽኑ ፍቅር ነው።

አንድ ክርስቲያን ፍቅረ እግዚአብሔር እንዳለው ወይም እንደሌለው ማወቂያው ባልንጀራውን መውደድ አለመውደዱን በማየት ነው። ባልንጀራን መውደድ እግዚአብሔርን ከመውደዱ ተለይቶ የሚሄድ አለመሆኑን

ሐዋርያው ቅዱስ ዩሐንስ ያስረዳናል። “ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህ ትዕዛዝ ከእርሱ አለን” 1ዮሐ 4፡20-21። የመንፈሳዊነትም መገለጫው እግዚአብሔርን ስለመውደድ በአንደበት ብቻ መናገር ሣይሆን እርሱ ሁሉን እንደወደደ እንዲሁ ባልንጀራን መውደድ መቻል ነው።

ሠ/ ጽኑ እምነት

እምነት በፍፁም ልብ እግዚአብሔርን ማመን ነው። መንፈሳዊ ሰው በእግዚአብሔር ላይ ጽኑ እምነት ያለውና ከራሱ ክብር ይልቅ የእግዚአብሔርን ክብር የሚያስቀድም ነው። በዚህም እግዚአብሔር ለእርሱ ያለውን ፍቅር በማሰብ በጊዜውም አለጊዜውም በቦታውም አለቦታውም ታማኝ ነው። በእግዚአብሔር ላይ ያለው ጽኑ እምነት እርሱንም ለእግዚአብሔር እንዲታመን ያደርገዋል እንጂ እግዚአብሔርን አይፈታተንም። እንዲሁም በእግዚአብሔር ላይ ያለው ጽኑ እምነት እርሱን ራሱን ለባልንጀራው እንዲታመን ያደርገዋል። በእግዚአብሔር የሚያምን ደግሞ ተስፋው እውን ይሆንለታል ሥራውም ይከናወንለታል “ሥራህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ አሳብህም ትፀናለች” ምሳ 16፡3፤ እንዲሁም “ልብህን ለእግዚአብሔር ብትሰጥ በእርሱም ብታምን ይደረግልሃል ደስተኛም ትሆናለህ” መዝ 37፡5 በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል።

ረ/ ፈሪሐ እግዚአብሔር

በመንፈሳዊ ሕይወት ጉዞ ላይ ከምድራዊ ነገር ይልቅ የመዳናችን ነገር የምናተኩርበት ሕይወት ነው። የዚህ ረጅም ጉዞ መጀመሪያው እግዚአብሔርን መፍራት ነው። “የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው” ተብሏልና ምሳ 7፡10። ከፈሪሐ እግዚአብሔር የደረሠ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግጋቱን የማይጥስና ትዕዛዛቱንም የማያፈርስ በመሆኑ ያለ ፈሪሐ እግዚአብሔር መንፈሳዊነት አይታሰብም። ፈሪሐ እግዚአብሔር ወደ ፍቅረ እግዚአብሔር የሚያደርስ መንገድ በመሆኑና ያለ ፍቅረ እግዚአብሔር ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ ሊያድር ስለማይችል የመንፈሳዊ ሰው መለያው እግዚአብሔርን መፍራቱ ነው። እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በሕይወት ዘመኑ ሁሉ የሚያስበው እግዚአብሔርን ብቻ ነው። ንግግሩ፣ አለባበሱ፣ አኗኗሩና በግልም ይሁን በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ በሚያደርገው ነገር በሙሉ ከስሜታዊ ፈቃድ ይልቅ እግዚአብሔርን ያስቀድማል በዚህም ጌታችን እንዳለው “እኔ ግን የምትፈሩትን አሳያችኋለሁ ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን እርሱን ፍሩ” ሉቃ 12፡5።

ሰ/ በጎ ህሊና ያለው

በጎነትን መስጠት የሚቻለው እግዚአብሔር ነው ያዕ 1፡17። “የሰው ልጅም ለክፋት አልተፈጠረም ለበጎ እንጂ፤ እንዲሁም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን” ሮሜ 8፡29 በማለት ያስረዳናል። የመንፈስ ፍሬዎችን ማፍራት የሚቻለው በጎ ኅሊና ሲኖር ብቻ በመሆኑ መንፈሳዊ ሰው መልካም ነገር ለማግኘት ኅሊናው በወረት ለጊዜው በፍርሃትና በሰዎች ጫና በይሉኝታ የተሞላ ሳይሆን በጎ ኅሊና ያለው ነው። የመንፈሳዊ ሰው በጎ ኅሊናው ነገርን ሁሉ ለመልካም የሚተረጉምና በጥበብ መንፈሳዊ

የሚኖር ነው። በምድራዊ አስተሣሠብ ዘር እየቆጠረ ቀለም እየለየ ተክለ ቁመና እየተመለከተ የሚያደርገው አልያም የማያደርገው አንዳችም ነገር የለም። ከክፋትና ከሥጋ ፈቃድ የራቀ በሰዎችና በስሜታዊ ሃሳብ ያልተዋጠ መከራ ቢፈራረቅበትም ለተንኮል የማይሸነፍ፣ በዘር በገንዘብና በተለያዩ ነገሮች ተገዶ የማይፈልገውን የማይመስለውን አይፈጽምም፤ ከኅሊናው ፈቃድ የሚፈጸመውን የሚያስበውን ሃሣብ እንከን የሌለበት በመሆኑ ይተጉበረዋል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን” ኤፌ 2፡10 በማለት በኅነትና መልካም ሥራ በእምነት በክርስቶስ የሚገኝ መሆኑን ያስረዳናል ክርስቲያን መሆን ለመልካም ሥራ ሁሉ ስለሆነና በኅነትም የመንፈስ ፍሬ እንደመሆኑ መጠን /ገላ 5፡22/ በኅኅሊና ከመንፈሳዊ ሰው የሚጠበቅ ነው።

ሸ/ መንፈሳዊ ቅናት ያለው

ለመልካም ሥራ የማይነሣሣ ሰው ለኃጢአት ቅርብ ነው፤ በዚህም የእግዚአብሔር ማደሪያ ስለሆነው ቤቱ ቅናት ስለሌለው ራሱን አሳልፎ ለጥፋት ይዳርጋል። ዓለምንም መከተል ይጀምራል። መንፈሳዊ ሰው ግን ሐዋርያዉ ቅዱስ ጳውሎስ “እርሱን ደስ የምናሰኝ ልንሆን እንቀናለን” 2 ቆሮ 5፡9 ብሎ እንደተናገረው በመንፈሳዊ ሕይወቱ ከጥፋት ይልቅ ለማደግ መንፈሳዊ ቅናት ያለው ነው። መንፈሳዊ ሰው የሚቀናው ቅናት ከሥጋ ሃሣብ የተለየ ነው። ምድራዊና የማያልፈውን ዓለም ክብር ረስቶ ከወገኖቹ ቅዱሳን ጋር መደመርን ሽቶ በመልካም ሥራ ላይ ተጋድሎን የሚጨምር ነው። በዚህም ለእግዚአብሔር ክብር የሚቀና እና ራሱን ከኅኅሊት የለየ ነው። መንፈሳዊ ቅናትን ገንዘብ በማድረጉም የራሱን ክብር ረስቶ አምላኩን የሚያስቀድም ከምድራዊ ሥራ የተለየ እና የሰማይ አባቱን ፈቃድ የሚያደርግ ነው።

ቀ/ አርአያነት ያለው

አርአያነት ለሌላው ምሳሌ መሆን ነው። የጌታችንም ሕይወት ለክርስቲያኖች ሁሉ ምሳሌ ነው፤ እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይም ለምሳሌነትና ለአርአያነት የተጠራ ነው፤ በቃልና በኑሮ ለሌላው ምሳሌ መሆን ደግሞ ትልቁ የክርስትና ሕይወት እድገት ነው። መንፈሳዊ ሰውም ለመልካም ሥራ ሁሉ በአርአያነት የሚጠቀስና በአርአያነቱም ለሌሎች ምሳሌ የሚሆን ነው። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ደቀመዝሙሩ ለሆነው ለጢሞቴዎስ ተናግሮታል “በቃልና በኑሮ፣ በፍቅርም፣ በእምነትም በንጽህናም ለሚያምኑት ምሳሌ ሁን” 1 ጢሞ 4፡12። ጢሞቴዎስም በእድሜ ደረጃ ገና ወጣት ቢሆንም ከልጅነቱ ጀምሮ በነበረው የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀትና በቤተሰቡ ዘንድ በተማረው እውነተኛ እምነት ለዚህ የመንፈሳዊ ሕይወት ምሳሌ መሆን የቻለ ነው 2 ጢሞ 1፡5 3፡15፤ ክርስትናም ለዚህ ታላቅ የሕይወት ምሳሌ ጭምር በመሆኑ መንፈሳዊ ሰው በእኒኢሩ ምሳሌ መሆን ይገባዋል።

የሰው ልጅ ከውድቀት በኃላ

1 ራቁታቸውን ሆኑ ማለታችን ነው ለነርሱ ከዚህ በፊት የጸጋ ልብስ ነበራቸው የሥጋ ልብስ የሌላቸውም ቢሆንም አይተፋፈሩም ነበር ትእዛዙን በሻሩ ጊዜ ግን ከእግዚአብሔር ጋር ተጣሉ ከሕይወትጋር ተጣሉ ፍቅር ቸርነት ህይወት የእግዚአብሄር ገንዘቦች ናቸው በዚህም የተነሳ ከጸጋ እግዚአብሔር ተለዩ አንድ ሰው ሐጢአት በሠራ

ቅጥር ጸጋው እየተቀነሰበት ሐጢአት እየቀረበው ይሄዳል አዳምና ሄዋን ተራቆቱ ሲባል ጸጋቸውን ተገፈፉ ማለት ነው ፍቅር የሐጢአትን ብዛት ይሸፍናል ፍቅር ከሌለ ግን በእግዚአብሔር ቸርነት ተሸፍኖ የነበረው ሐጢአት ይገለጣል።

2 ኃይላቸውን አጡ ለምን ቢባል ሐጢአት የሰውን ኃይል ያሳጣልና ዘፍ **3 6** ዘፍ **30 37 -43**

3 ሰላማቸውን አጡ በገነት ያለው ሁሉ የሚያስደስትና ሰላም ሚሰጥ ነበር ዘፍ 2 1 እጸበለስን በበሉ ጊዜ ግን ክፋትን ከማየት ተሰውሮ የነበረው ዓይናቸው ተከፈተ ስለዚህም በሰላም ይኖሩ የነበሩት አዳምና ሄዋን ተፋፈሩ ሰላምን አጡ ወደ ቻካም ገብተው በፍርሀት ተሸሸጉ ዘፍ 3 8

4 ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው የፍቅር ግንኙነት ተቋረጠ ።

5 መርገምን አመጡ ይህም መርገም ያመጣባቸው ጣጣ ።

ሀ ነጻነታቸውን አጡ ሞትን ወይም ሕይወትን የመምረጥ መብት ነበራቸው ኋላ ግን ያለአማራጭ ሞትን ተቀብሎ ሕይወትን ንጉሥነትን የመምረጥ መብታቸውን አጡ ቀድሞ ንጉሥ የነበረ አዳም የሐጢአት ባርያ አገልጋይ ሆነ ሐጢአትን የሚሠራ ሁሉ የሐጢአት ባርያ ነውና ይሕ የሐጢአት ባርነት እስከ ልጆቻቸው ተላለፈ ሮሜ 5 15

ለ ሕይወታቸውን አጡ ቀድሞ ለዘለዓለም በሕይወት ይኖሩ ዘንድ ተሰጥቶቸው ነበረ በኋላ ግን በበደላቸው ምክንያት ሞት መጣባቸው ሕይወታቸውንም አጡ

ሐ እግዚአብሔርን መምሰል አጡ ቀድሞ በእግዚአብሔር አርአያ ተፈጥሮ እግዚአብሔር የባሕርይ ገሸ እንደሆነው ሁሉ አዳምም የጸጋ አምላክ ሆኖ ምድራውያን ፍጥረታትን ሁሉ እንዲገዛ ተሰጥቶት ነበር ከዚህ ወዲያ ግን በበደሉ ምክንያት ይህን ሁሉ አጣ

መ ባለ አዳዎች ሆኑ ማንም ሊከፍለው የማይችለው ሞት ባለ አዳ ሆኑ ይህንንም አዳ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ትውልድ በሙሉ ሊከፍሉት አልቻሉም ።

ሠ የገነት በር ተዘጋባቸው ገነት ለአዳምና ለሄዋን የተሰጠች በረከት ነበች እግዚአብሔር እንደሌሎች ፍጥረታት ፈጥሮ ሳይተው እንደቤተ መንግሥት ያለች ገነትን ሠራላቸው በበደለ ጊዜ ግን ራሱን ከእንስሳት ጋር በማስተካከሉ ከገነት ወጣ እንስሳት ወደሚኖሩበት ወደዚህም ምድር ተሰደደ ዘፍ 3 1

ወስብሐት ለእግዚአብሔር